# አዲስ ዘመን

ኢፕድ
ማክሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 063 ኅዳር 3 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# ተኪ የኬሚካል ምርት ለኢንዱስትሪው ዕመርታ

**ታደሠ ብናልፈው**

በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች 48 ነጥብ ሁለት አልሙኒየም ስልፌት፤ 22 ነጥብ አራት ስልፈሪክ አሲድና አምስት ነጥብ አንድ ሀይድሮጅን ፐር አክሳይድ እንደሚጠቀሙ በቅርብ ጊዜ የተደረገ ጥናት ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም አምራች ኢንዱስትሪዎች 81 በመቶ የሚሆነውን የኬሚካል ምርት የሚያገኙት ከሀገር ውስጥ የኬሚካል አምራች ፋብሪካዎች ሲሆን ሶስት በመቶ የሚሆናቸውን ከውጭ የሚገቡት ምርቶችን ይጠቀማሉ፤

ተኪ የኬሚካል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ግንባታ አፈጻጸም 82 በመቶ ደረሰ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- 120 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው የአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታው አፈጻጸም 82 በመቶ መድረሱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ 120 ሜጋ ዋት ሃይል የማመንጨት አቅም እንዲኖረው ታስቦ እየተገነባ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡ የንፋስ ሃይል ማመንጫ ግንባታ ፕሮጀክት በአሁኑ ጊዜ አፈጻጸሙ ላይ 82 በመቶ ደርሷል፡፡

የግንባታ ሥራው ደረጃ በደረጃ እየተሠራ መሆኑን ያነሱት አቶ ሞገስ ፤ በዚህም ስምንት ክላስተር ያላቸው 80 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የሚያስችሉ የንፋስ ተርባይኖች ተከላ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ አሁን ላይ

የአይሻ የንፋስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ረቂቅ አዋጁ የውጭ ባንኮች በፋይናንስ ዘርፉ እንዲሠማሩ የወጣውን ፖሊሲ ወደ ተግባር የሚያሸጋግር ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጁ መንግሥት የፋይናንስ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ለማድረግ የወጣውን ፖሊሲ ወደ ተግባር እንደሚያሸጋግር ተገለጸ፡፡

ረቂቅ አዋጁ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ‹‹ህብረብሔራዊ አንድነትን ለመገንባት ሀገራዊ መግባባቱ አስኳል ነው››

- አቶ አገኘሁ ተሻገር የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ብዝኃ ማንነት ላላት ኢትዮጵያ ህብረብሔራዊ አንድነትን ለመገንባት ሀገራዊ መግባባቱ አስኳል ነው ሲሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አቶ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ፡፡

19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ህዳር 29 "ሀገራዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ በደቡብ ኢትዮጵያ በአርባ ምንጭ ከተማ ይከበራል፡፡ በመሪ ሃሳቡና ህብረ ብሔሄራዊ አንድነትን በሚያጠናክሩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለሚዲያ አመራሮችና ለጋዜጠኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሥልጠና ማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ ንግግር ያደረጉት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አቶ አገኘሁ ተሻገር እንደገለጹት፤ እንደ ኢትዮጵያ ብዝኃ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ባህልና አመላካከት ላላት ሀገር ህብረብሔራዊ አንድነትን ለመገንባት ሀገራዊ መግባባቱ አስኳል ነው። በዓሉ የኢትዮጵያ ብዝኃ ማንነት ዕውቅና ከመስጠት



በላይ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትንና ሰላም ለማጽናት ይረዳል፡፡

የፌዴራል ሥርዓትን በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባትና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመነጋገርና በመመካከር በመፍታት ህብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አገኘሁ ገለጻ፤ በዓሉ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዕርስ በርስ ትውውቅና የባህል ልውውጥ መድረክ ነው፡፡ እንዲሁም የክልሎች መሠረተ ልማትና ኢንቨስትመንት እንዲነቃቃ የሚያደርግ ነው፡፡

የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከፍፃሜ ለማድረስ ሕዝባዊ ንቅናቄ እንዲፈጠር የሚያደርግ መሆኑን ጠቁመው፤ በአስተናጋጅ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችና ታሪካዊ ቦታዎች እንዲተዋወቁ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

ህብረብሔራዊ አንድነት ያለ ሀገራዊ መግባባት አይጸናም ያሉት አፈ ጉባዔው፤ ሀገራዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት መሠረቱ ነው፡፡ ሀገራዊ መግባባት በውይይት፣ በምክክር፣ በሰጥቶ መቀበል የሚመጣና ለጋራ እሴቶች ክብርና ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የወል ትርክቶች ተሰናስነውና ተዋሕደው ሲፈሱ

"ህብረብሔራዊ አንድነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# አሳሳቢው የውሻ እብደት በሽታ

**ውብሸት ሰንደቁ**

**ዜና ሀተታ**

በዛብህ ደሳለኝ በውሻ እብደት በሽታ (ራቢስ) በተያዘ ውሻ በመነከሱ በለጋ ዕድሜው ከ45 በላይ መርፌዎችን በዕምብርቱ እንዲወስድ ተገድዷል፡፡ መርፌው በወቅቱ ካስከተለበት ስቃይ በላይ አሁን ድረስም ቅዝቃዜ እና ብርድ ሲያገኘው ስለሚያመው ልብስ ደራርቦ መልበስ ያዘወትራል፡፡ ተሸፋፍኖ መሄድንም እንደሚመርጥ ይናገራል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስኮ አካባቢ ነዋሪ የሆነው በዛብህ በልጅነት ዕድሜው በውሻ ዕብደት በሽታ በተያዘ ውሻ መነከሱ ዛሬም ድረስ የጤና ዕክል አስከትሎበታል፡፡ ነገሩን የከፋ አድርጎ ያባባሰው ደግሞ የነከሰው ውሻ በውሻ ዕብደት በሽታ እንደተያዘ አለመታወቁ ነበር፡፡

ውሻው በበሽታው እንደተያዘ ባለመታወቁ የበዛብህ ወላጆች ወደሕክምና ከመውሰድ ይልቅ በቸልታ ያልፉታል። ጉዳዩ ውሎ ሲያድር ልጁ ላይ የህመም ምልክት በመታየቱ ወደ ሕክምና ወሰዱት፡፡

በወቅቱ በዛብህን የመረመሩት የሕክምና ባለሙያዎች ሕፃኑ በራቢስ በሽታ መያዙን ተናግረው፤ በሕይወት የመትረፉ ዕድል 50 በመቶ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በዚህም የሕፃን በዛብህ አባት እንዲወስኑ ተደርጎ ሕክምናው ተጀመረ፡፡

አሁን በዛብህ አድጎ እና ሥራ ይዞ አዲስ አበባ ውስጥ የመንግሥት ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡

በኮሪደር ልማቱ መዲናዋ ውብ መሆኗ ቢያስደስትም በየመንገዱ የውሾቹ ነገር የሚታዩት ውሾች ጉዳይ ግን ሊታሰብበት ይገባል ይላል፡፡

በምሽት የእጅ ባትሪ ይዞ መሄድን ግድ ይሉ የነበሩ የመዲናዋ መንገዶች አሁን ላይ ፍንትው ብለው ብርሃናቸውን ፈንጥቀዋል። እየሰነፈጡ ለጉንፋን ይዳርጉ የነበሩ ጎዳናዎቿ ወደ ጠረናቸው ማራኪ ሆኗል። ሆኖም ወትሮ በየመንገድ የሚንገላወዱ ውሾችና መንደሮች ሲፈርሱ ማደሪያ ያጡ ውሾች ግን ዛሬም አሉ፡፡



በመዲናዋ ለመናፈስ የወጣ ከተሜ ምቹ የእግረኛ መንገድና የመዝናኛ ቦታዎች ተገንብተውለታል። ይሁንና ባለቤት አልባ ውሾች እዚህም እዚያም የመታየታቸው ጉዳይ ደግሞ ሊታሰብበት እንደሚገባ በዛብህ ይናገራል።

ሚሊዮችን የያዘችው አዲስ አበባ ፤ ከነዋሪዎቿ መሳ ለመሳ የሚኖሩ 400 ሺህ ባለቤት አልባ ውሾችም እንዳሏት መረጃዎች ያመላክታሉ።

አያድርገው እና የውሻ ዕብደት በሽታ (ራቢስ) አልያም ሌላ በውሾች የሚተላለፍ ወረርሽኝ ቢከሰት ተጠቂ የሚሆነው ሰፊው ሕዝብ ነው። በግብርና ሚኒስቴር የቬተርነሪ ፐብሊክ ሄልዝ ዴስክ ኃላፊ ሲሳይ ጌታቸው (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የውሻ ዕብደት በሽታ ትኩረት ከተነፈጋቸው በሽታዎች ውስጥ አንዱ ነው ፡፡

በሽታው ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ተናግረው፤ በዓለም ላይ ከ150 ሀገራት ውስጥ በሽታው እንደሚገኝ፤ በአህጉር ደረጃ ሲታይም በአፍሪካና በኤዥያ የሚገኘው አብላጫውን እንደሚይዝ ይጠቅሳሉ፡፡

አስከፊው ሁኔታ ደግሞ መቶ በመቶ ገዳይ በሽታ መሆኑ ነው ሲሉም ያክላሉ፡፡ በሽታው ከ15 ዓመት በታች ያሉ ህፃናትና ታዳጊዎችን እንዲሁም ሴቶችን ማጥቃቱም ሌላ የበሽታው አስከፊ ገፅታ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

አንድ ሕፃን በውሻ ዕብደት በሽታ ከተለከፈና በጊዜው ሕክምና ካልወሰደ በአካባቢው የሚያገኘውን ነገር እየነከሰ፤ ራሱን ከአገኘው ነገር ጋር እየፈጠፈጠ ለሞት የሚዳረግበት ሁኔታ ይፈጠራል ሲሉ በሽታው ከበሽታነቱ ባሻገር ማኅበረሰባዊ ሥነልቦና ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

የውሻ ዕብደት በሽታ በክረምትም ሆነ በበጋ የሚመርጠው ጊዜ አለመኖሩን በመጥቀስ፤ በወረርሽኝ መልክ በየትኛውም አጋጣሚ ሊነሳ ይችላል ይላሉ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የውሻ ዕብደት በሽታን እኤአ እስከ 2030 ድረስ ለማጥፋት የተቀመጠ ግብ መኖሩን ጠቁመው፤ በኢትዮጵያም ግቡን ለማሳካት የተቀረፀ ስትራቴጂ እየተተገበረ እንደሚገኝ ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ በአዲስ አበባም ይህ ስትራቴጂ የሚተገበር ይሆናል ይላሉ።

የውሻ ባለቤትነትንና የውሻ ብዛትን መቆጣጠር በዚህ ስትራቴጂ አንዱ የውሻ ዕብደት በሽታን ለማጥፋት የሚደረግ ርምጃ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ የባለቤት አልባ ውሾች ቁጥር 400 ሺህ እንደሚደርስ መገመቱን እንደሚጋሩት፤ ከውሾች ተፈጥሯዊ የመራባት ሂደት በተጨማሪ በከተማዋ በየጊዜው በሚሠሩ ልማቶች የሚኖሩበትን አካባቢ በሚለቁ ዜጎች ምክንያት የባለቤት አልባ ውሾች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱም አስጊ እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

በዚህም ልማት የሚያሠራ አካል ዜጎች የሚኖሩበትን አካባቢ ሲለቁ ውሾቻቸውን ይዘው እንዲዘዋወሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መግባት ላይ መደረሱን ጠቅሰው፤ ሂደቱንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆነን እንደግፋለን ይላሉ፡፡

ሆኖም በአሁኑ ወቅት መንገድ ላይ ውሾች በብዛት ይታያሉ፤ ይህን ቁጥር መቀነስ ተገቢ በመሆኑ ጉዳዩን የተመለከተ ዕቅድ መያዙንም ያነሳሉ፡፡ ያረጁና የታመሙ ውሾችን ዓለም አቀፍ የእንስሳት ሕግ በሚፈቅደው መልኩ የሚወገዱበት መንገድ እንደሚመቻች ነው የሚናገሩት፡፡

ሌሎች ውሾች ደግሞ ባለቤት እንዲኖራቸው እየተሠራ መሆኑን ከእነዚህ ርምጃዎች የሚተርፉት ውሾች ዓለም አቀፍ ሕግን ባከበረ መልኩ እንደሚወገዱ አብራርተዋል፡፡ በዚህ ዓመትም ይህ ሥራ የሚጀመር መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የውሻ ቁጥር ወደ ሰባት ሚሊዮን እንደሚገመት ጠቁመው፤ በሽታውን ከሀገር ለማጥፋት ለአምሥት ተከታታይ ዓመታት 70 በመቶ የሚሆነውን የውሻ ብዛት መከትብ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

# ስምምነቱ የመዲናዋን ሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ለማሻሻል የሚያስችል ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚረዳውን መተግበሪያ ለማልማት ከአራት ተቋማት ጋር ተፈራረመ።

ስምምነቱ በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት፣ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ መካከል ተፈርሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የስምምነቱ ዋና ዓላማ ባለፉት ሁለት ዓመታት ኤጀንሲው ሲጠቀመው የነበረበት መተግበሪያ (ሶፍት ዌር) ማሻሻል ነው። ይህም ነዋሪዎች ፈጣን የዲጂታል አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል።

አዲስ አበባን ስማርት ከተማ ለማድረግ ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በዚህም አንላይን የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር በማስቻል ቀልጣፋና ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ለመዘርጋት ታቅዷል ያሉት አቶ ዮናስ፤ ይህም ሕገወጥ ተግባራትን ለመቅረፍ እና የመዲናዋን ነዋሪዎች በቁጥር ለመለየት እንደሚያስችል ገልጸዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የመተግበሪያውን ደህንነት፣ ተደራሽነት እና ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ከሳይበር ደህንነት አንፃር ይፈትሻል። በዚህም የሀገር ውስጥ አቅምን በማሳደግ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 እውን ለማድረግ እንደሚሠራ የገለጹት ደግሞ የአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ትዕግስት ሀሚድ ናቸው።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሰው ሠራሽ አስተውሎት አጠቃቀም እና የሥራ ውጤታማነት ላይ ማማከሩን ኢንስቲትዩት እንደሚሠራ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሰለሞን አማረ



በበኩላቸው፤ በመዲናዋ የሚሰጡ አብዛኛው አገልግሎቶች ከሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ጋር የተያያዙ ናቸው። በተለይ ከፋይናንስ አገልግሎቶች ጋር ያለውን የዲጂታል ትስስር ለማጠናከር የመሠረተ ልማትና የሶፍት ዌር ማሻሻያ ማድረግ አስፈልጓል። ለዚህም ሀገር በቀር አልሚ ድርጅት ይመረጣል ነው ያሉት።

ዲጂታል መታወቂያ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲጠናከር ያደርጋል። ይህም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩል ሚና ይጫወታል ያሉት የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮዳሄ አርአያ ሥላሴ፤ ስምምነቱ የዜጎችን ተጠቃሚነት መሠረት ያደረገ ነው ብለዋል።

በተለይ የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህም የሀገሪቱ ዲጂታል ኢኮኖሚ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድርም ገልጸዋል።

በመዲናዋ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ማሻሻያ ላይ ኢንሳ እና የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የማማከር ሥራውን የሚያከናውኑ ሲሆን ብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ደግሞ የፋይዳ መታወቂያ አቅምን ያሳድጋል። ይህም ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 እውን የማድረግ ጉዞ አካል መሆኑ በወቅቱ ተገልጿል።

# የቡና ጥራትን ለማሳደግ ለአርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ድጋፍ እየተደረገ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አርሶ አደሩ ዘመናዊ የቡና ምርት ማዘጋጃ አሠራርና መሣሪያዎችን በመጠቀም የምርት ጥራትን እንዲያሳድግ የተጠናከረ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ገለፀ፡፡

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ የቡና ልማት እና ጥራት ዳይሬክቶሬት አቶ ታከለ ኃይለማሪያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ መንግሥት የቡና ምርትና ጥራትን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ከፍ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው።

ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ለአርሶ አደሩ የቡና ምርት ማዘጋጃ ዘመናዊ አሠራሮችን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ ዘመናዊ መሣሪያዎች በስፋት እየቀረቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

አርሶ አደሩ ከዚህ ቀደም ቡና ለማምረት የሚጠቀምበት ባህላዊ መሣሪያዎችና አሠራሮችን የመቀየር ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተው፤ ቡና ለመጎንደል እና ለመቁረጥ የሚፈጀውን ጉልበትና ጊዜ ለመቆጠብ በርዳታ የተገኙት ዘመናዊ የመጎንደያና የጉድጓድ መቆፈሪያ ማሽኖች ለአርሶ አደሩ እንዲከፋፈል መደረጉን ተናግረዋል።

ለረጅም ዓመታት ምርት የሰጡ የቡና ዛፎች በማርጀታቸው ምርትና ጥራት ላይ ችግር መፍጠሩን አስታውሰው፤ ችግሩን ለመቀነስ አዳዲስ ችግኞችን የመትከልና የመንከባከብ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን አንስተዋል።

በተጨማሪ የምርት ማበልፀጊያ መሣሪያዎች በመንግሥት በኩል ለአርሶ አደሩ እንዲዳረስ መደረጉ የቡና ምርት እና ጥራት እንዲጨምር ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሀገሪቱ ከሚመረተው ቡና አብዛኛው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እንደሚዘጋጅ የገለፁት አቶ ታከለ፤ በክልሉ ከሶስት ሚሊዮን በላይ ሔክታር መሬት ላይ ቡና እየለማ መሆኑን አስታውቀዋል።

በክልሉ የቡና ልማት ምርታማነቱ በሔክታር ከስድስት ነጥብ አምስት ኩንታል ወደ ዘጠኝ ኩንታል ማሳደግ መቻሉን አመልክተው፤ ተጨማሪ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል። በዚህም የቡና ምርት እና ወደ ውጭ የመላክ አቅም እየጨመረ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡

የቡና ምርት ጥራትና ለመጨመር የሚሠሩ ሥራዎች ደግሞ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ከፍ ለማድረግ አይነተኛ ሚና እንዳላቸው አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም አምራቾች በቀጥታ ለውጭ ገበያ ቡናን እንዲያቀርቡ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ አቶ ታከለ ገለፃ፤ አምራቹ ራሱ ወደ ውጭ ሲልክ በገበያ እና በአምራቹ መካከል ያሉት ደላሎች ይቀንሳሉ። በሥራ ላይ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ የቁጥጥር አሠራር በመዘርጋቱ ለውጦች እየታዩ ይገኛል፡፡

# በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለማጽናት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ስምምነት ተደረገ

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ያደረጉት ስምምነት በሀገሪቱ ዴሞክራሲን ለማጽናት በሚደረገው ጥረት አንድ ርምጃ ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል መሆኑን የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ አስታወቀ፡፡

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት በትናንትናው እለት ተፈራርመዋል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንት አቶ ዛዲግ አብርሃ እንደገለጹት፤ ስምምነቱ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በመፍጠር በሀገሪቱ ዴሞክራሲን ለማጽናት በሚደረገው ጥረት አንድ ርምጃ ወደፊት ለማራመድ ያስችላል፡፡

ሀገራቱ መድበለ ፓርቲ ሥርዓት በኩል እያደረገች ያለውን ልምምድ እንዲሳካ እና ችግሮችን በመቅረፍ ወደፊት የምትራመድ ሀገር ለመገንባት የአመራር ልማት ሥራ አስፈልጊ መሆኑን አንስተው፤ የአመራር ብቃት ሥራ ከተሠራ የሚሳካና ስምምነቱም ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው አስታውቀዋል።

እንዲሁም ከዚህ ቀደም በአካል ተቀራርበው



የማያውቁና ከሩቁ እንደ ባላንጣ ይተያዩ የነበሩ ከተፎካካሪና ከገዢ ፓርቲ አመራሮች በጋራ የአንድ አመራር ልማት ፕሮግራም ሥልጠና የሚወስዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሚያሣልፉት የሥልጠና ጊዜያትም የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እርስ በዕርስ እንዲተዋወቁ በማድረግ ከፍተኛ የባህል ሽግግር ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር የአመራር ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በሚፈጠረው የባህል ሽግግርም በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው አስታውቀዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር ብቃት የአንድ ሀገር የህልውና ጉዳይ መሆኑን አቶ ዛዲግ አንስተው፤ በዚህም ብቁ አመራር በመፍጠር በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ እና ለባህል ለውጥ መልካም እድል ይፈጥራል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፖርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ደስታ ዲንቃ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ በጋራ ምክር ቤቱ በዋነኝነት የያዘውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዓላማና በሀገሪቱ መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ለመገንባት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለማሳካት ጉልህ ሚና እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ምክር ቤቱ የኢትዮጵያን ኋላቀር የፖለቲካ ባህል በመቀየር ዘመናዊና ጊዜውን የሚመጥን የፖለቲካ ባህል ለመገንባት ዓላማ በመያዝ በሀገሪቱ ከ60 በላይ የሚሆኑ ሀገር አቀፍና ክልላዊ ፓርቲዎችን ይዞ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በስምምነቱም የጋራ ምክር ቤት አባላቶቹ የአቅም ግንባታ ትምህርቶችና ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ የተለያዩ የምክክር መድረኮችንና ሰነዶችን ለማዘጋጀት እንዲሁም ጥናትና ምርምር በማካሄድ የጋራ ምክር ቤቱ የያዛቸውን ዓላማዎች የማሳካት የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡



# በክልሉ ከአንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሚገኝ ሰብል ተሰብስቧል

## - ከመኸር አዝመራ ከ337 ሚሲዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በመኸር አዝመራ በተለያየ ሰብሎች ከለማው 11 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝ ሰብል መሰብሰብ መቻሉን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በአጠቃላይ ከመኸር አዝመራ ከ337 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠበቅም ተመላክቷል፡፡

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 የምርት ዘመን በመኸር አዝመራ ከ11 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በሰብል የተሸፈነ ሲሆን ከዚህም ውስጥ አንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የለማ ሰብል ተሰብስቧል፡፡

እንደ አቶ በሪሶ ገለጻ፤ ከአንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሚገኝ የደረሱ ሰብሎች ወቅቱን ባልጠበቀው ዝናብ እንዳይበላሹ በደቦና በቤተሰብ እንዲሁም ኮምባይነሮችን በስፋት በማሠማራት መሰብሰብ ተችሏል።

በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የደረሱ ሰብሎችን የሰው ሃይል እና ኮምባይነር በመጠቀም እየተሰበሰበ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሰባሰቡ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ሰብሎቹ ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሰው ሃይልን በማሳተፍና ኮምባይነርን በመጠቀም እየተሰበሰበ እንደሚገኝና ሥራው በሚቀጥሉት ቀናትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

እስካሁንም ስንዴ፣ ሩዝ፣ በቆሎና የቅባት እህል የተሰበሰበ ሲሆን ከተሰበሰቡ ሰብሎችም 16 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ምርት መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡

በመኸር አዝመራ ከለማው ሰብል ውስጥ ስንዴ፣ በገብስ፣ በጤፍ፣ በቆሎ፣ በሩዝ፣ ማሽላና የተለያዩ ሰብሎች እንደሚገኙበት እንደሆነ አስረድተዋል።

በአጠቃላይ ከመኸር አዝመራ ከ337 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ የምርት ብክነትን በሚቀንስ መልኩ ሰብል የመሰብሰብ ሥራው መጠናከሩን ተናግረዋል።

የዝናብ ስርጭቱ ከቦታ ቦታ የተለያየ በመሆኑ የሰብል አሰባሰቡ የአየር ሁኔታውን መሠረት ባደረገ መልኩ እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አርሶ አደሩ ሰብል በሚሰበስብበት ወቅት ዝናቡን በመፍራት ያልደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ እንደሌለበት አቶ በሪሶ ተናግረዋል፡፡ የሰብል ብክነት እንዳያጋጥም በሰብል አሰባሰብ ሥራው ሁሉም ባለድርሻ አካል መሳተፍ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

# ሕገወጥ የምግብና መድኃኒት ምርቶችን ለመቆጣጠር የተጠናከረ ትብብር ያስፈልጋል

ነፃነት አለሙ

አዲስ አበባ፡- ሕገወጥ የምግብና መድኃኒት ምርቶችን ለመቆጣጠር የተጠናከረ ትብብር እንደሚያስፈልግ የአዲስ አበባ ከተማ ምግብ መድኃኒት ባለሥልጣን ገለፁ፡፡

ተቋሙ ትናንትና ባዘጋጀው ከተማ አቀፍ ፎረም ምሥረታ ላይ የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ትዕግስት በዳዳ እንደተናገሩት፤ ሕገወጥ የምግብና መድኃኒት ምርቶች በጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመቀነስ ትብብሮችን ማጎልበት ይገባል፡፡



በርካታ ሕገወጦች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ እስካለን ድረስ ችግሩን መቶ በመቶ ማጥፋት ባንችልም ህብረተሰቡ፣ የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች በጋራ ከሠራን ችግሩን መቀነስ እንችላለን ብለዋል፡፡

ሕገወጥ ምርቶች የሚሠሩት በየጓዳውና በድብቅ ቦታዎች ውስጥ ነው ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጇ፤ እኔም ለጤናዬ ባለሥልጣን ነኝ ብለን ሁላችንም ከተንቀሳቀስን ሕገወጥነት ከስር መሠረቱ መከላከል እንችላለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የምግብ ደህንነቱ መጠበቁን ማረጋገጥና የጤና ተቋማትን አገልግሎት በተመለከተ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት እንዲሁም መቆጣጠር የባለሥልጣኑ ኃላፊነት ቢሆንም ችግሩ እያንዳንዱን ሰው ስለሚነካ በመሆኑ የሁሉንም ርብርብ እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል፡፡

የባለሥልጣኑ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር መብራቶም ጣዕመ በበኩላቸው፤ "እኔም ለጤናዬ ባለሥልጣን ነኝ" በሚል መሪ ሃሳብ የጤና ቁጥጥር ፎርም መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

የፎረሙ አላማ ለከተማው ነዋሪ በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣ ሕገወጥ ምርቶችን መቆጣጠር፣ የተፋጠነና የማይቆራረጥ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት መገንባት፣ በሕገወጦች ላይ ስለተወሰዱ ርምጃዎች ማሳወቅን እንደሚያጠቃልል ገልፀዋል፡፡

ውስብስብ ባህሪ ያለውን ሕገወጥነት ለመከላከል የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑም ለፎረሙ አስፈላጊነት እንደ አንድ ምክንያት መቀመጡን ጠቅሰዋል፡፡

የቁጥጥር ፎረም ሰነዱ ህብረተሰቡን በባለቤትነት ስሜት ሕገወጥ የምግብና መድኃኒት ምርቶችን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት እንዲያጎለብት ይረዳል ብለዋል፡፡

የፎረሙ አባላት ባለሥልጣኑን ጨምሮ የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት፣ የንግድ ማህበረሰብ አደረጃጀቶች፣ የጤና ባለሙያዎች ማህበር፣ የሕዝብ አደረጃጀቶች፣ የመንግሥት አካላት፣ የምክር ቤት ተወካዮች፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን እንዲሁም የሲቪክና በጎ አድራጎት ማህበራትን ያካተተ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

# የአይሻ የንፋስ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

80 ሜጋ ዋት ኃይል ወደ ብሄራዊ የኃይል ቋት የማስገባቱ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

የተቀረውን 40 ሜጋ ዋት ኃይል ወደ ቋት ለማስገባት የሚያስችሉ የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ቢሆንም ተርባይኖችን የመትከል ሥራው በፋይናንስ አቅርቦት ምክንያት ለሁለት ዓመታት ባለበት እንዲቆም ተደርጎ እንደነበር አውስተዋል፡፡

አሁን ላይ ግን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አበዳሪዎችን ሳይጠብቅ በራሱ ፋይናንስ ግንባታውን ለማካሄድ ወስኖ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ገልጸዋል ፡፡

የአይሻ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የንፋስ ሃይሉን ወደ ሃይል ቋት በማስገባት ሃይል ለሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ስርጭት የሚደረግ ይሆናል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ አዳማ የሚገኙት ሁለት ፕሮጀክቶች እንዲሁም በአሸጎዳ ያለው የንፋስ ሃይል ማመንጫን ጨምሮ አይሻ አራተኛ የንፋስ ሃይል ማመንጫ ነው፡፡ ካሉት የንፋስ ማመንጫ ውስጥም አይሻ ውጤታማ ሊባል የሚችል ነው ፡፡

የአይሻ ፕሮጀክት እየተገነባበት ያለው አካባቢው ከባህር ለሚነሳ ንፋስ ቅርብ በመሆኑ ተርባይን የማንቀሳቀስ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ከሌሎቹ በአንጻራዊነት ሲታይ ፕሮጀክቱ የተሻለ ኃይል የማመንጨት አቅም እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ዳይሬክተሩ፤ ፕሮጀክቱ በአካባቢው አልሚዎች ኢንቨስት እንዲያደርጉ እድል ፈጥሯል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው መንግሥት በቅርቡ ከአሚያ ፓወር ጋር የተፈራረመው ስምምነት መሆኑን በአብነት ጠቅሰዋል። በስምምነቱ መሠረትም የግል አልሚዎቹ እስከ 300 ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጭ ፕሮጀክት ለመገንባት ማቀዳቸውን አንስተዋል፡፡

ይህም እንደ ሀገር ከንፋስ መጠቀም ያለብንን የኤሌክትሪክ ኃይል እንድናገኝ ያደርጋል ብለው በተጨማሪም ተቋሙ በቀጣይ በተለያዩ አካባቢዎች የንፋስ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

# ‹‹ህብረብሔራዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ህብረብሔራዊአንድነትንእንደሚገነቡ አመልክተው፤ በአንፃሩ የእኔ ባህል፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት በአጠቃላይ የእኔ ማንነት ብቻ የበላይ ይሁን የሚለው ነጠላ ትርክት ህብረ ብሔራዊ አንድነት እውን እንዳይሆን ያደርጋል ብለዋል፡፡

አንድነቷ ያልተጠበቀና ሰላሟ ያልሰፈነ ሀገር ልማቷን ማሳካት አትችልም ያሉት አቶ አገኘሁ፤ በዓሉ የጋራ ታሪኮችንና እሴቶችን የምናሳይበት፣ የሕዝቦች የኑሮ መስተጋብር የሚበለጽግበት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

19ኛው የብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በየደረጃው ሲከበር የሕዝቦችን አንድነትና ትስስር እንዲረጋገጥ በማድረግ እንዲሁም የሀገራችን ሰላምና አንድነት ተጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ በትኩረት የምንሠራበት ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የመገናኛ ብዙኃን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በፍትሐዊነት፣ ህብረብሔራዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመገንባት ላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበው፤ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል ሲከበር በሕዝቦች መካከል በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ለማድረግ መገናኛ ብዙኃን የማይተካ ሚና አላቸው ብለዋል አቶ አገኘሁ፡፡

# ተኪ የኬሚካል ምርት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

16 በመቶ የሚሆነውን ደግሞ ከሀገር ውስጥም የሚመረቱና ከውጭም የሚገቡ የኬሚካል ግብዓቶችን እንደሚጠቀሙ ጥናት ይጠቁማል፡፡

አምራቾች ከውጭ ተመርቶ የሚመጣ የኬሚካል ግብዓት የሚጠቀሙበት ምክንያት 51 ነጥብ አንድ በመቶ ከሀገር ወስጥ የተሻለ የዋጋ ቅናሽ ያለው በመሆኑ አመልክተው፤ የሀገር ውስጥ አምራቾች 22 በመቶ በተፈለገው መጠን ያህል ምርት ፤ 15 በመቶ የጥራት ችግር ስላለባቸው፤ 10 ነጥብ ሶስት በመቶ የሚሆኑት ሀገር ውስጥ መመረቱን አለማወቃቸው መሆኑን ጥናቱ ያብራራል፡፡

ኢትዮጵያ ከውጭ የሚገቡ የኬሚካል ምርቶችን በተኪ ምርቶች በመተካት የኢንዱስትሪ፤ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ግብዓት በማሟላት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ በትኩረት እየሠራች መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከውጭ የሚገባን የተለያየ የኬሚካል ግብዓትን በሀገር ውስጥ በማምርት ኢንዱስትሪዎች የኬሚካል ምርት በቀላሉ እንዲያገኙና በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ እየተከናውነ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በሀገር ውስጥ ሶስት አይነት የኬሚካል ግብዓቶች እየተመረቱ ነው፤ ቀሪ የኬሚካል ምርቶችን ለማምረት የፋብሪካዎችን ማሽኖች የማደስና የመቀየር፤ በቴክኖሎጂን የማስደገፍ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ በዘርፉ የተሠማሩ ባለሙያዎች ያብራራሉ፡፡

የኬሚካሎች ግብዓቶች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ የተራዘመ የትራንስፖርት ሂደት እንደሚያጋጥም፤፡ የተራዘመ የትራንስፖርት ሂደት መኖሩም የአገልግሎት ጊዜያቸው እንዲያልፍ ወይም ለማለፍ እንዲቃረብ ምክንያት መሆኑ ይነሳል፤ ይህም በኢንዱስትሪዎች፤ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደረ መሆኑ ይገለጻል፡፡ ይህና መሰል ችግሮችን ለመፍታት ኢትዮጵያ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የሚል ንቅናቄ በመፍጠር እየሠራች ትገኛለች የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ ይጠቁማል፡፡

የአዋሽ መልካሳ የኬሚካል ፋብሪካ የምርት ጥራቱንና የማምርት አቅሙን ለማሳደግ የኬሚካል ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ምርምርና ልማት ማዕከል ባስጠናው ጥናት የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች በብዛት ሶስት አይነት የኬሚካል አይነቶችን ማለትም አልሙኒየም ሰልፌት፤ ሰልፈሪክ አሲድና ሃይድሮጂን ፐር ኦክሳይድንን እንደሚጠቀሙ ይዳስሳል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የኬሚካል ክላስተር ዳይሬክተር ወይዘሮ አስማ ረዲን ለኢፕድ እንዳብራሩት፤ የማኑፋክቸሪግ፤ የኢንዱስትሪ በአጠቃላይ አምራች ዘርፉ የኬሚካል ግብዓት ተጠቃሚ ነው፤ የአምራች ዘርፉን ለማሳደግ የኬሚካል ግብዓትን ሙሉ ለሙሉ በሀገረ ውስጥ የመሸፈን እየተሠራ ነው፡፡ ኬሚካሎችም በሀገር ውስጥ መመረታቸው ተጠቃሚዎች በቅርበት ምርቶችን እንዲያገኙ ከማድረግ ባለፈ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል ይላሉ፡፡

ከውጭ ሀገራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲከሰት ከማድረጋቸው በተጨማሪ የትራንስፖርት ሂደታቸው የተራዘመ ነው፤ የትራንስፖርት ሂደታቸው የተራዘመ መሆኑም አገልግሎት ጊዜያቸው የሚያልፍበት አልያም አጭር ጊዜ የሚሆንበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ይህም በኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚፈጥረው አሉታዊ ጫና ከፍተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ኬሚካሎች በሀገር ውስጥ መመረታቸው ኢንዱስትሪዎች ከስር ከስር እየተጠቀሙ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፤ ኬሚካሎችን በጥራት ለማምርት በትኩረት መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

በአዋሽ መልካሳ የኬሚካል ፋብሪካ ሶስት አይነት የኬሚካል ግብዓት የማምረት ሥራ እየተከናወነ ነው፤ እየተመረቱ ያሉ የኬሚካል ግብዓቶችም ለኢንዱስትሪዎች ቀላል የማይባል ሚና እየተጫወቱ ነው፤ ተጨማሪ ኬሚካሎችን ለማምረት የትራንስፎርሜሽ ፕሮግራም ተቀርፆ እየተሠራ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

የአዋሽ መልካሳ የኬሚካል ፋብሪካ ማምረት ከጀመረ 20 ዓመታትን አስቆጥሯል፤ ፋብሪካ ያለውን አቅም ተጠቅሞ የኬሚካል ምርትና ምርታማነቱን እንዲያሳድግ የአረጁ ማሽኖችን የማደስ፣ በቴክኖሎጂ የማስደገፍ፤ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ የማድረግ ተግባር እያከናወነ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

የሀገር ውስጥ የኬሚካል ግብዓት በማምርት ላይ የተሠማሩ ፋብሪካዎችን ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙና የተሻለ ምርት እንዲያመርቱ የማድረግ ተግባር እየተከናወነ ነው፡፡ የኬሚካል አምራች ፋብሪካዎች በቴክኖሎጂ መደገፋቸውም ጥራት ያለው ምርት አምርተው የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት አልፈው ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ያደርጋቸዋል ሲሉ ይናገራሉ። ይህም የሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ የራሱ ድርሻ አለው ባይ ናቸው፡፡

ለኢንዱስትሪዎች የተለያዩ የኬሚካል ግብዓት የሚያቀርቡ ኬሚካል አምራች ፋብሪካዎች ወደ ላቀ ትርንስፎርሜሽን እንዲሻገሩ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን የመሳብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር ሐድጉ ኃይለኪሮስ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኬሚካል ግብዓት ለኢንዱስትሪ፤ ለማኑፋክቸሪንግ፤ ለግብርናው በአጠቃላይ ለሁሉም አምራች ዘርፍ እድገት ወሳኝ ነው፤ ለሁሉም አምራች ዘርፍ ወሳኝ የሆነውን የኬሚካል ምርት በሀገር ውስጥ የማምረት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ለኢንዱስትሪዎች የኬሚካል ግብዓት በቅርበትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ እንዲቻል የሀገር ውስጥ የኬሚካል ፋብሪካዎችን የማምረት አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ይላሉ፡፡

አብዛኛው የሀገር ውስጥ የሚገኙ የኬሚካል ፋብሪካዎች እያመረቱት ያለው ግብዓት ካላቸው አቅም በታች ነው፡፡ የኬሚካል አምራች ፋብሪካዎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እንዲያመርቱና ከውጭ የሚገባን የኬሚካል ግብዓት በሀገር ውስጥ መተካት እንዲችሉ የቴክኒካል ድጋፍ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

የሀገር ውስጥ የኬሚካል ፋብሪካዎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እንዲያመርቱ ያለባቸውን ማነቆ በየወሩ በጥናት የመለየት፤ ለችግሩ መፍትሔ የመስጠት፤ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግና የማምረት አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነውም ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች ያላቸውን የማምረት አቅም ተጠቅመው የሀገር ውስጥ ፍላጎትን እንዲያሟሉ፤ ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ የሚያደርግ ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡

የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪው በብዛት ሶስት አይነት የኬሚካል አይነቶችን ማለትም አልሙኒየም ሰልፌት፤ ሰልፈሪክ አሲድና ሀይድሮጂን ፐር ኦክሳይድንን ይጠቀማል ሲሉ ጥናቱን ያቀርቡት የኬሚካል ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ምርምርና ልማት የገበያ ምርምር ልማት ዴስክ ሃላፊ አቶ አሉላ በቀለ አመልክተው፤ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች 48 ነጥብ ሁለት በመቶ አልሙኒየም ስልፌት፤ 22 ነጥብ አራት በመቶ ስልፈሪክ አሲድ ፤ አምስት ነጥብ አንድ በመቶ ሀይድሮጅን ፐር ኦክሳይድ እየተጠቀሙ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎች 81 በመቶ የሚሆነውን የኬሚካል ምርት የሚያገኙት ከሀገር ውስጥ የኬሚካል አምራች ፋብሪካዎች ነው፤ ሶስት በመቶ የሚሆናቸውን ከውጭ ይጠቀማሉ፤ 16 በመቶ የሚሆነውን ደግሞ ከሀገር ውስጥም ከውጭም እየተጠቀሙ ነው ሲሉ በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

ሙሉ ለሙሉ ኬሜካሎችን ሀገር ውስጥ ለማምረት የፋብሪካዎቹን አቅም ለመገንባት የተሰጠው ትኩረት ፈርጀ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ይሆናል፡፡

# ረቂቅ አዋጁ የውጭ ባንኮች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደሚያሸጋግር ተገለጸ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅና የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ተወያይቷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ እንደገለጹት፣ የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጁ የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በመንግሥት የተወሰነውን ፖሊሲ ወደ ተግባር ለማሸጋገር የሚያስችል ነው፡፡

በህብረተሰቡ ዘንድ የባንኮች ተአማኒነት ጠንክሮ እንዲሄድ ዘርፉ በሕግ ማዕቀፍና በአዋጅ መደገፍ አለበት ያሉት ሰብሳቢው፣ የሕግ ማዕቀፉ ከዓለም አቀፍ የባንኮች ሥራ አኳያ የተቃኘና ከሀገሪቱ የሕግ ሁኔታዎች ያገናዘበ ሆኖ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ የፋይናንስ ዘርፉን ዘመናዊ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቅሰው፣ ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በእውቀት፣ በክህሎት ለመደገፍ፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን ለማሳደግ፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ በመፍጠርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመደገፍ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

የውጭ ባንኮች ከሀገር ውስጥ ባንኮች ጋር አብረው በመሥራት በቴክኖሎጂ፣ የአቅምና ክህሎትን በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንደሚደግፍም አመላክተዋል፡፡

የብሔራዊ ባንክ ገዢ ማሞ ምህረቱ በሰጡት ማብራሪያ እንደተናገሩት፣ ረቂቅ አዋጁ መንግሥት በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ የውጭ ኢንቨስትመንትን የፈቀደ በመሆኑ አዋጁ ፖሊሲውን ወደ ተግባር የሚያሸጋግር ነው፡፡

የውጭ የባንኮች በፋይናንስ ዘርፍ ተሰማርተው ለኢኮኖሚው እድገት ቀጣይነት ያለው አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያስችል አዋጅ ነው ያሉት ገዢው፣ የውጭ የፋይናንስ ተቋማት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲገቡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርትና አካሄዶች ምንድናቸው? የሚለውን የሚለይ ነው ብለዋል፡፡

የባንክ ሥራ አዋጅ ከ16 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለክለሳ እንደተዘጋጀ በመግለጽ፣ ረቂቅ አዋጁ አዳዲስ ባንኮች ወደ ዘርፉ ሲቀላቀሉ ሊያሟሉ ስለሚገባቸው መስፈርትና ፍቃድ አሰጣጥ ሂደቱን የሚወስን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ በፍቃድ አሰጣጥን፣ አካሄዱንና የውጭ ባንኮችን አመራረጥ ሂደትን እንደሚያሳይ ጠቅሰው፣ ባንኮች ቀውስ ቢያጋጥማቸው ብሔራዊ ባንክ እንዴት መፍትሄ መስጠት እንዳለበት የተደራጀ ሥርዓትንም ያበጀ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የፋይናንስ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት የማድረግ እሳቤ በመንግሥት በኩል ውሳኔ አግኝቷል ያሉት ገዢው፣ የዘርፉ ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግ ዘርፉ ከፍ እንዲልና ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

የኢኮኖሚውን የብድር ፍላጎቶች ማሟላት የሚያስችሉ ባንኮች ወደ ሥራ ሲገቡ የኢኮኖሚ እድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ እንሠማራለን ብሎ ሁኔታውን ያሟላና የጠየቀ ሁሉም ባንክ ፍቃድ እንደማይሰጠው በመግለጽ፣ ብሔራዊ ባንክ እንደ ኢኮኖሚው ሁኔታ እያየና የፋይናንስ ዘርፉን ተጽዕኖ እየገመገመ እንደ ሁኔታው ፍቃድ እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በባንክ ሥራ ውስጥ ለመሳተፍ ከሚቻልባቸው አንደኛው መንገድ የውጭ ባንኮች ከሀገር ውስጥ ባንኮች ጋር በቅንጅት መሥራት መሆኑን ገልጸው፣ የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጭ ባንኮች ጋር በፈቀዱት ልክ በቅንጅት እንዲሠሩ የሚበረታታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ቋሚ ኮሚቴው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን ለብሔራዊ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቤኑና መንደር የለውጡ ሌላው ትሩፋት ነው!

ኢትዮጵያ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከፍተኛ አቅም ካላቸው ሀገራት መካከል ትመደባለች ፤ ተስማሚ የአየር ጸባይ ፤ ውብ መልካምድር፤ የብዙ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ልዩ ልዩ ባህሎች መገኛ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤትም መሆኗም ይህን ያመላክታል።

የቀደምት ሥልጣኔ እና የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ያላትና የብዙዎችን ቀልብ የሚስቡ የታሪክ ትርክቶች ባለቤት ነች ፤ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን ቀድማ ማስተናገድ የቻለች ፤ የእምነት ተቋማቱ ምእመናንም ተቻችለው እና ተስማምተው ለዘመናት አብረው የኖሩባት ፤ ዛሬም የሚኖሩባት ሀገር ነች ።

ይሁንና እነዚህን ለቱሪዝም እንዱስትሪው ትልቅ አቅም የሆኑ ሀብቶችን አውቃ እና አልምታ በአግባቡ መጠቀም ሳትችል ኖራለች። ይህንን እውነታ ለመቀየር የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣበት ማግስት ጀምሮ ሰፊ ጥረት አድርጓል፤ በዚህም አስደማሚ ተጨባጭ ውጤቶችንም ማስመዝገብ ችሏል።

የቱሪዝሙን ዘርፍ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት እንደ አንድ ስትራቴጂክ አቅም አድርጎ በፖሊሲ ደረጃ የወሰደው መንግሥት ፤ በዘርፉ ያለውን ሀብት "ማወቅ ፣ ማልማት እና መጠበቅ" በሚል መሪቃል ወደ ሥራ በመግባት ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን እምቅ አቅም ገልጦ ማሳየት በሚያስችል ትልቅ መነቃቃት ላይ ይገኛል፡፡

ለዚህም ባለፉት አምስት ዓመታት በገበታ ለሸገርና ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የእንጦጦ ፣ የአንድነት እና የወዳጅነት ፓርክን በአዲስ አበባ ፤ ከአዲስ አበባ ውጪም የጎርጎራ ፣ የወንጪ ፣ በኮይሻ ፕሮጀክት የሀላላ ኬላና የዝሆን ዳና ሎጅ ፓርኮችንና ሪዞርቶችን በአጭር ጊዜ በጥራት ተገንብተው ወደ ሥራ የገቡበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። በገበታ ለትውልድ ደግሞ በተለያዩ ክልሎች ሌሎች ተመሳሳይ የቱሪስት መዳረሻዎች እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ ፓርኮች ግንባታ ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜ በማራዘም እና ሀገሪቱ ከቱሪስቶች የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ የሚቻል ሲሆን፣ ለበርካታ ዜጎች አዲስ የሥራ እድል መፍጠርም ተችሏል፡፡ የሀገሪቱን የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች በማስፋት ዘርፉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የተሻለ አበርክቶ እንዲኖረው ትልቅ አቅም መፍጠር እየቻለ ነው።

ግንባታዎቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሆኑ የውጭ ኢንቨስተሮች በዘርፉ መዋለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ የተሻለ መመነቃቃት የሚፈጥሩ ፤ ሕዝቡም አጠገቡ ያሉ ትኩረት ሳይሰጣቸው የኖሩ ሀገራዊ ሀብቶች ለምተው ሀገር እና ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚችሉ ተጨባጭ ተሞክሮ እየቀሰመባቸው ያሉ ናቸው።

ከትናንት በስቲያ በግሉ ዘርፍ እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግሥት ትብብር ተገንብቶ ለምረቃ የበቃው የቤኑና መንደር የዚሁ እውነታ ሌላኛው ማሳያ ሲሆን፣ በዘርፉ የተመዘገበ ሌላ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት እንዲሁም የይቻላል ሀገራዊ መነቃቃታችን መገለጫም ነው ።

መንደሩ በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ አካባቢ በሰቃ ሀይቅ ዳርቻ የተመሠረተ ሲሆን፣ እጅግ ዘመናዊ መኝታ ክፍሎች፣ አዳራሽ፣ ሲኒማ ቤት፣ የመዝናኛ ሥፍራዎች፣ ስፓና ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ ግንባታዎች የተካሄዱለትም ነው፡፡

የሌማት ትሩፋት አንዱ ሥራ የሆነው የፍራፍሬ ልማት የተካተተበት መሆኑም፣ ግብርናን ከቱሪዝም መዳረሻ ጋር ለማስተሳሰር ትምህርት የሚወሰድበት ያደርገዋል። ባህላዊ የኪነ-ህንጻ ጥበብን ከዘመናዊ ግንባታ ጋር አቀናጅቶ የያዘ፤ ለአካባቢው ተጨማሪ የቱሪዝም አቅም የፈጠረ ውብ መዳረሻ ነው።

ግንባታው ከሁሉም በላይ በጣም አስቸጋሪ የሆነውን የአካባቢውን የአየር ሁኔታና መልከዓ ምድር በመቋቋም እውን መደረጉ፤ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ ሀገርን በትጋት መለወጥ እንደሚቻል ትምህርት ሰጥቷል፤ በቀጣይ ለሚገነቡ ተመሳሳይ ፕሮጀክት የይቻላል መንፈስን ያጎለብታል።

በመንግሥት በኩል ሀገራዊ የቱሪዝም አቅሞችን አውቆ ለማልማት የሚደረገው ጥረት እና እየተመዘገበ ያለው ተጨባጭ ውጤት ፤ ለዘርፉ ተገበውን ትኩረት ሰጥቶ ከግሉ ዘርፍ ጋር ተባብሮ መንቀሳቀስ ከተቻለ፤ ከዘርፉ ሀገር እና ሕዝብ ገና ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በተጨባጭ ያሳየ ፤ የለውጡ አንዱ ትሩፋት ነው ።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እንደ ንስር አሞራ ራስን የማደስ ፈተና

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ)**

ኢትዮጵያ በርካታ የጀግንነት ታሪኮች ያሏት፤ የሥልጣኔ በር ከፋች ፤ አክሱም እና ላሊበላን ... የመሳሰሉ እጅግ ውብና ከዘመኑ የቀደሙ አስደናቂ የኪነ ህንጻ ግንባታዎች ባለቤት የሆነች ፤ ልዩ ልዩ ጠቢባን የፈለቁባት ፤ በቀኝ ግዛት ያልተገዛች ፣ የራሷ ፊደል ያላት ፤ ዛሬ ያደጉ ለምንላቸው ሀገራት ድጋፍ ስታደርግ የነበረች የቀደሙ ሥልጣኔዎች ባለቤት ናት።

"የት ይደርሳል የተባለው ..." ሆኖ የትናየት መድረስ ያለባት ሀገር አሁንም በድህነት ከዚህ በሚመነጭ ጠባቂነት ውስጥ ነች ። እውነታው በብዙ መልኩ ሲገለጽ ያማል። እነሱ ከፍታ ላይ ሆነው የእኛ ካለንበት ወርዶ መገኘት ያንገበግባል። አሁን ላይ ክስተቱን ቆም ብሎ ማሰብ የግድ ይላል።

ያለፈ የጀግንነት ታሪክን እያወደሱ መኖር ብቻ የትም አያደርስም ፣ በባለፈው ድክመታችን እያላዘኑ ሁሉን ድሮ ቀረ ብለን ድሮ ላይ መቆም ታሪክን አይቀይርም። ታሪክ የሚቀየረው ታሪክ ቀያሪ አስተሳሰብ ላይ ቆመን መንቀሳቀስ ስንችል ብቻ ነው። ይህን ሳስብ የንስር አሞራ ተፈጥሮ ትዝ አለኝ ። ንስር አሞራ አርባ ዓመታት በጥንካሬ ከኖረ በኋላ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች ይገጥሙታል። እንደልቡ መብረር አይችልም ፣ በጥንካሬው ልክ አይዘልቅም ፤ ክንፋም ጥፍሩም መንቁሩም መድካማቸውን እድሜ ቆጥረው ያበስሩታል።

እነዚህን ፈታኝ የሆኑ ነገሮችን ማለፍ ከቻለ የኖረውን ያህል እድሜ ደግሞ መኖር ይችላል። ፈተናውን በድል መወጣት ካልቻለ ግን ሕይወቱ ያልፍና ታሪኩ በመጀመሪያው 40 ዓመቱ ይደመደማል።

ንስር አሞራ እድሜው በአጭሩ እንዳይቀጭ ከባድ የሆነውን መስዋዕትነት ለመክፈል እራሱን ያነሳሳል። ከመኖሪያ አካባቢው ርቆ እና ከዘመድ አዝማዱ ተለይቶ ወደ አንድ ተራራ ጫፍ ይወጣል ፤ ጭካኔ በተሞላበት መልኩ አርጅቶና ተቆላሞ ምግቡን አላስበላ ያለውን መንቁሩን ከአለት ጋር አጋጭቶ ይነቅላል። መንቁሩ እስኪያድግለት ድረስ ህመሙን ታግሶ ረሃቡን ችሎ ይቆያል።

መንቁሩ ሲያድግለትና ሲጠነክርለት ደግሞ ምግቡን ፈልጎና ፈልፍሎ እንዳያገኝ ያደረገውን ያረጀውን ጥፍሮቹን በመንቁሩ አማካይነት ጭካኔ በተሞላው መንገድ መንቅሎ ይጥላል። ጥፍሮቹ እስኪያድጉለት በተለመደው ስቃይ ውስጥ ያሳልፋል። ጥፍሮቹ ጊዜያቸውን ጠብቀው ከበቀሉለት በኋላ ደግሞ ሌላውን አላስበርር ብሎ የከበደውን ክንፉ ላይ ያለውን ያረጀ ላባውን እያራገፈ ከላዩ ላይ ይጥላል።

ላባው እስኪያድግለትም መስዋትነት እየከፈለ ይቆያል ፤ ይራባል፣ ይጠማል ፣ በቁስሉ ይንገበገባል። ከዛም ላባው መብረር በሚያስችለው ደረጃ ላይ ሲደርስ እራሱን ሙሉ ለሙሉ ማደሱን አረጋግጦ ሌላ ረጅም ዓመታትን በሰላምና በደስታ ለመኖር አዲስ ሕይወት ይጀምራል።

የኢትዮጵያውያንም ሁኔታ ልክ እንደ ንስሩ አሞራ ሊሆን ይገባል ። ቀደም ሲል በሀገራችን የነበሩ የተሠሩ ታሪኮቻችን የንስር አሞራ የወጣትነት ዘመን ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል። ያ ዘመን በነበረበት ጥንካሬ አልቀጠለም። ብዙ ነገሮች ወደኋላ በሚመስል መልኩ ቀርተዋል።

ለእድገቷ ጸር የሆኑ ነገሮች ስንፍና ፣ ሙስና፤ መገፋፋት ፤ሴራ ፣ መልካም ነገርን አለማድነቅ፣ መጥፎውን አለማውገዝ ... በዝተው ህልውናዋን አደጋ ውስጥ ከተውታል። እንደቀደመው ዘመን ወደከፍታ መብረር እንዳትችል አድርገዋታል። ካለችበት የህልውና ስጋት ለመውጣት ለልማትና ለብልጽግና ጸር የሆኑትን ሁሉ አራግፋ ወደ ከፍታ መብረር እንድትችል ራሷን ማደስ ይጠበቅባታል።

በልማት ለመቀየር ፣ቴክኖሎጂ ለመታጠቅ ዓለም የደረሰበት ብልጽግና ላይ ለመድረስ ዛሬ እንደ ንስር አሞራው የማይቀረው መስዋዕትነት መክፈል አለበት። ይህንን ብልጽግና እንደሚፈልግ ፤ ዳግም ከፍታውን እንደሚናፍቅ ሕዝብ በአግባቡ ልንረዳው ይገባል።

**በልማት ለመቀየር፣ቴክኖሎጂ ለመታጠቅ ዓለም የደረሰበት ብልጽግና ላይ ለመድረስ ዛሬ እንደ ንስር አሞራው የማይቀረው መስዋዕትነት መክፈል አለበት። ይህንን ብልጽግና እንደሚፈልግ ፤ ዳግም ከፍታውን እንደሚናፍቅ ሕዝብ በአግባቡ ልንረዳው ይገባል**

በሽታን ለማከም የሚደረገ የቀዶ ጥገና ህመም እንዳለው ሁሉ ወደ ብልጽግና እና የቀደም ከፍታ የሚደረግ የሀገር ጉዞም ህመም አለው ። በህክምና ሂደት ውስጥ ያለ ጣር ፈውስን ለማጽናት እንደመሆኑ፤ ሀገርን በማሻገር ሂደት የሚፈጠርም የዜጎች የሕይወት መጎረባበጥም ግቡ የተሻለች ሀገር መፍጠር ነው ።

የኮሪደር ልማትን በምሳሌነት እንየው። የኮሪደር ልማት እንደ ንስር አሞራ ሁሉ ለከተማዋ እድገት ፤ ለነዋሪዎቿ ምቾት ፈተና የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ መልክ ማስያዝ ነው ፤ ለዚህ ሲባል የሚፈርሱ አካባቢዎች፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአካባቢያቸው የሚፈናቀሉ ዜጎች ይኖራሉ።

የለመዱትን አካባቢ የኖሩበትን ማህበራዊ ሕይወት መተው ያስገድዳል። ይሄ በማህበራዊ ሕይወት ለረጅም ዓመታት ተሳስሮና ተጋምዶ ለኖረ ማህበረሰበ ከባድ ፈተና መሆኑ አይቀርም ። ግን ደግሞ ለተሻለ ሀገራዊ ጉዳዮች ይሄንን ሁሉ ህመም ታግሶና ችሎ ማለፍ ያስፈልጋል።

አላራምድ ያለውን እንቅፋት ከፊት ለፊት አንስቶ ወደፊት መራመድ ካልተቻለ ነገም ወሬው ከድህነት በታች የሚለው ተረት ተረት ይሆናል። ለነገ ለልጆቻችን የምናተርፈው አዲስ ነገር አይኖርም። የበለጸጉ ሀገራት ከማለት ባለፈ በብልጽግና ላይ ቆመን መናገር አንችልም።

ሀገር በቀደመ ታሪክ ብቻ አትኖርም ፤እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ዘመኑን የሚመጥን ታሪክ ሠርቶ ማለፍ ይጠበቅበታል ። ይህም ትውልድ በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ ነው።

አሁን የምናየው የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት የንስሩ አሞራ እራስን የማደስ አንድ ክፍል ነው። ሌሎች የሚገነቡ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ሠርቶ ማጠናቀቅ ደግሞ የንስር አሞራ ሌላው እራስን የማደስ ክፍል ነው። እንደ ንስር አሞራው ሶስተኛ እና አራተኛ እያሉ ሀገርን ማደስ ያስፈልጋል። ሁሉንም ነገር ለማደስ የሚደረገው ጥረት ግን አልጋ በአልጋ ሳይሆን ብዙ ጥርስ የሚያስነክሱ ህመሞችን በጽናት ማስታመም የሚጠይቅ ነው።

የሠለጠነ ሀገር ያደገው በዚሁ መልኩ ነው። እንደ ንስር አሞራ ራሱን በብዙ ስቃይ ውስጥ አድሶ ነው ። ለእዚህ ደግሞ ሁሉም እራሱን ማዘጋጀት እንደ ሀገርም ተባብረን መቆም ይኖርብናል። ዛሬ ያደከመን ፣ ያሰለቸን የልማት እንቅስቃሴ ነገ ሙሉ ሆኖ እንደሚያስደስተን ዛሬ ላይ ቆም ብሎ ማሰብም ተገቢ ነው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የስንዴን ስኬት በሌሎች ሰብሎች ለመድገም

**ታሪኩ ዘለቀ**

አፈርን የማልማት፣ ሰብልን የማምረትና እንስሳትን የማርባት ጥበብ "ግብርና" ይሰኛል:: ግብርና፤ የእጽዋትና የእንስሳት ምርቶች ለሰዎች ጥቅም ይውሉ ዘንድ ማዘጋጀትና ለገበያ ማቅረብንም ያካትታል:: ቻይና፣ አሜሪካ፣ ግሪክ፣ ሜሶፖታሚያና ሱመራዊያን ግብርናን በመጀመርና በማዘመን ታሪክ ውስጥ ቀዳሚነትን ይወስዳሉ:: የኤፍራጠስና የጢግሮስ ወንዞች ለዓለም የግብርና እና የሥልጣኔ ታሪክ ምንጭ ሆነው ይጠቀሳሉ::

ከዘመን ዘመን በርካታ የለውጥ ደረጃዎችን እያሳለፈ የመጣው ግብርና፣ በእጅ ከሚካሄድ ቁፋሮ ተነስቶ፣ እንጨትን በመቅረጽና ብረትን በማቅለጥ የተሠሩ መሣሪያዎችና ሌሎችንም ዘዴዎች አልፎ በ16ኛውና 19ኛው ክፍለ ዘመን መካከል እንግሊዝ በዘመናዊ ግብርና የላቀ ምርት እድገት እንድታስመዘግብ አድርጓል:: ዛሬም ይህ ዘርፍ በየዘመኑ በሚፈጠሩ ቴክኖሎጂዎች እየታገዘ የምግብ ዋስትናችንን እንድናረጋግጥ ረድቶናል::

እ.ኤ.አ. በ1843 ሳይንሳዊ የማዳበሪያ ምርምር ከመጀመሩም ባሻገር እንደ ሶዲየም ናይትሬትና ፎስፌት ያሉ ማዳበሪያዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችም ተገንብተዋል። ግብርና በከፍተኛ ደረጃ መዘመን በታየበት፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በ1901 የመጀመሪያው በቤንዚን የሚሰራ ትራክተር ከተመረተ በኋላ የግብርና ሥራ በፍጥነትም በጥራትም ማደግ ችሏል:: በመካናይዜሽንና በምርምር እየበለፀገ የመጣው ግብርና ከመነሻው አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የሰው ልጅ መሬትን አልምቶ፤ እንስሳትን አልምዶ ህልውናውን ያስቀጥልበት ዘንድ ከተፈጥሮ የተሰጠው ስጦታው ነው ማለት እንችላለን::

ባለንበት ዘመን፣ በሀብት የበለጸጉ ሀገራት የረቀቀ ግብርናን የመወዳደሪያ ዘርፍ አድርገውታል፤ በየጊዜው ለሚከሰቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮችም በምርምር የታገዘ መፍትሔን እየሰጡ ተጉዘዋል:: በዚህም ሕዝባቸውን ከመመገብ አልፈው ለሌሎችም መትረፍ ችለዋል::

ግብርና ለኢትዮጵያም የህልውናዋ መሠረት፤ ገበሬውም የሕዝቧ የዘመናት ባለውለታ ነው:: የተለያዩ ዝርያዎችን ለማብቀል ምቹ የሆነ ሥነ ምህዳርንም ታድላለች:: ዶ/ር አስናቀ ፍቅሬ፣ «ግብርናችን ሥልጣኔው ከእኛ እስከ ነጩ አብዮት» (2010 ዓ.ም.) በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት፣ ኢትዮጵያ እድሜ ቆጠር ማረሻን ፈልስፋ 100 ሚሊየን እስክንደርስ ለነበሩት 1ሺህ 500 ዓመታት መግባናለች:: በአሁኑ ሰዓትም 17 ሚሊየን ያህል አርሶ አደሮች 100 ሚሊየን ኢትዮጵያውያንን ይመግባሉ::

መጽሐፉ እንደሚናገረው፣ ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብትም ሆነ በሰው ኃይል ያላት አቅም በቀላሉ ምርታማ መሆን የሚያስችላት ነው:: ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ ግብርናችን መዘመንን ይሻል:: ግብርናችንን የማዘመኑ ጉዞ ረጅም ርቀት የሚቀረው ቢሆንም፣ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ዘርፉ በጉልህ የሚታዩ ለውጦችን እያስመዘገበ ይገኛል::

**ዳግመኛ ስለልመና እንዲሁም ስለረሃብ ማሰብን ተረት ለማድረግ የዜጎች ጓዳ ሙሉ ሆኖ ረሃብን ከምድር ላይ በዘላቂነት ማጥፋት የጊዜው ተቀዳሚ አጀንዳ ሆኗል**

ኢትዮጵያ በተለይም ባለፉት ስድስት ዓመታት በግብርና ምርታማነት ላይ ስትራቴጂካዊ ለውጥ በማምጣት ሰፋፊ ድሎችን አስመዝግባለች። በኢትዮጵያ የሚታረስ መሬትን በእጥፍ በመጨመር ምርታማነትን ማሻሻል ተችሏል። በተለይ በስንዴ፣ በጤፍ፣ በቆሎ እና ገብስ ምርቶች ላይ ተጨባጭ ለውጥ ተመዝግቧል። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 230 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተመርቷል። በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር አማካኝነትም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ውጤታማ ሥራ ተከናውኗል:: በመርሃ ግብሩም 40 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል።

ይህ ተጨባጭ ውጤት የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት(ዩኒዶ)፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እና የዓለም የምግብ ድርጅት(ፋኦ) በጋራ ያዘጋጁት ከረሀብ ነፃ ዓለም /world without hunger/ ጉባኤ በኢትዮጵያ እንዲካሄድ መንስኤ ሆኗል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ ይህ ጉባኤ ኢትዮጵያን ተመራጭ ያደረገው በለውጥ መንገድ ላይ መሆኗን ተከትሎ የመጣ ነው ይላሉ። መሠረታዊውን የጉባኤውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ጉባኤው ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄዱ ትርጉሙ ሰፋ ያለ ነው:: ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በተለይ በምግብ ራስን ለመቻል በጣም ሰፊ ሥራዎች ሰርታለች:: በዚህ ሂደትም ደግሞ ብዙ ሀገራት ሊማሩበት የሚችሉ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችላለች:: በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና አግኝታበታለች::

ጉባኤው እዚህ መካሄዱ አንድም በዚህ ዘርፍ ያከናወነቻቸው ሥራዎች ለሌሎች ሀገራት የምታቀርብበትን ትልቅ እድል ፈጥሮላታል:: በዛውም ደግሞ በሂደቱ ያጋጠሟትን ፈተናዎች የምትቀርፍበትን መንገድ ከሌሎች ሀገራት ልምድ የወሰደችበት ትልቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ነበር::

በጉባኤው ላይ የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ዳይሬክተር ገርድ ሙለር እንደገለፁት ኢትዮጵያ ምግብ ከመቀበል ወደ ምግብ መላክ ተሸጋግራለች:: ይህ ምስክርነት ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ታሪክ ነው:: ይህ ንግግር እንደዚሁ ጉንጭ ለማልፋት ወይም በምላስ ወለምታ የተነገረ አይደለም::

በመዝገበ ቃላት ጭምር የረሃብ ምልክት እስከ ማድረግ ደርሰው ከነበሩት፤ ምግብ ረዳናት ሲሉ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በመግለጫዎች ያጨናንቁ ከነበሩ ተቋማት መካከል የተንፀባረቀ ነው:: ውጤቱም የኢትዮጵያዊያን ጀግና አርሶ አደሮች የላብ ወዝ ነው፤ ስንዴ ልማት ሲል አቋሙን በቁርጠኛ ተግባር የገለጸው የመንግሥት ሥራ መሆኑ ግልፅ ነው::

ባለፈው እኤአ ሐምሌ 2023 አልጀዚራ ኢትዮጵያ ስንዴ ከዩክሬን የተላከላት አስመስሎ እስከ መዘገብ ደርሶ ነበር:: ይህንን ዘገባቸውን ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማንሳታቸው ይታወሳል:: ኢትዮጵያ ምግብ ተቀባይና የምትረዳ እንጂ በጠንካራ ሥራ ልትቀየር የምትችል ሀገር መሆኗን ለመግለጽ የሚተናነቃቸው ጥቂት አይደሉም። ሰርታ በተግባርም አሳይታ ስንዴ ከውጭ አላስገባም ማለቷ የጎረበጣቸው ብዙ ነበሩ::

ታዲያ የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ገርድ ሙለር ንግግር ክብደት እዚህ ጋር ዋጋው ይታያል:: ኢትዮጵያ የምግብ ላኪ ሆናለች:: ይህን እውነታ ዓለም እንዲረዳው ከረሀብ ነፃ የዓለም ጉባኤን ማስተናገዳችን የሰጠን የመጀመሪያ ትሩፋት ሊባልም የሚችል ነው::

ኢትዮጵያ ለዜጎቿ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ውጤታማ ሥራ ሰርታለች:: ነገር ግን በምግብ ሥርዓቱ ላይ ምርታማነቱን በመጨን፣ በማሰራጨትና ፍጆታ ላይ አሁንም የሚመጡ ፈተናዎች አሉ:: ምርታማነትና የምርት ስብጥር፣ በግብዓት እጥረት ምክንያት እየተጓተቱ ነው:: በአፈር ማዳበሪያ፣ ችግኞችና ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ምክንያት:: በተጨማሪም የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የእርሻ መስፋፋት ለመሬት መሸርሸር እና ለደን መጨፍጨፍ ምክንያት እየሆነ ነው:: ለዚህ ችግር እንደመፍትሔ የሚጠቀሰው የበካይ ጋዝ ልቀትን መቀነስ እንደሆነ ይነገራል::

ባለፉት ስድስት ዓመታት በግብርናው ሽግግርና ምርታማነት በተሰጠው ትኩረት በሰብል የተሸፈነው መሬታችንን በማሳደግ ለምርታማነቱ የተሰጠው ትኩረትም ሰብሉን ፍሬያማ እያደረገው ነው:: ድርቅን መቋቋም ያስቻሉ እንደ ስንዴ፣ጤፍ፣ በቆሎና ማሽላ ያሉ ሰብሎች ላይ ምርታማነቱ ጨምሯል:: እንደ አረንጓዴ ዐሻራ ያሉ ከአምስት ዓመታት በፊት የተጀመሩ ሥራዎች የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል የሚያስችሉና የግብርናውን ምርታማነት የሚያሳድጉ መርሃ-ግብሮች እንደሆኑ ይታመንባቸዋል:: በእነዚህ ጊዜያትም 40 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል::

ኢትዮጵያ የግብርና ምርትንና ምርታማነትን የማሳደግ ተሞክሮዋ ከረሃብ ለመውጣት ወሳኝ ርምጃ መሆኑን የዓለም ከረሃብ ነፃ መውጣት ጉባኤ ተሳታፊዎች ተናግረዋል:: በዓለም አቀፉ ጉባኤ የታደሙ ጉባኤተኞች እንዳሉት እሴት መጨመርና ለዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ ቀጣይ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል::

ዳግመኛ ስለልመና እንዲሁም ስለረሃብ ማሰብን ተረት ለማድረግ የዜጎች ጓዳ ሙሉ ሆኖ ረሃብን ከምድር ላይ በዘላቂነት ማጥፋት የጊዜው ተቀዳሚ አጀንዳ ሆኗል። በምግብ ራስን ከመቻል በዘለለ ከሚትረፈረፈው እርሻ ለሌሎች ማካፈልና ጥጋብ የሚለው ቃል በአንደበት ላይ ታትሞ ይቀር ዘንድ ነው የሚፈለገው:: በኢትዮጵያ ለሶስት ቀን ቆይታ የነበረው ዓለምን ከረሃብ ነፃ የማድረግ ጉባኤ የግብርና ምርትን በማሳደግ፣ ምርት ላይ እሴትን በመጨመር ዘርፈ ብዙ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባ አፅንኦት የተሰጠበት ነው::

ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየሄደችበት ያለው መንገድ የሚደነቅ ነው:: ምርት እንዲትረፈረፍ ውጤታማ በሚያደርግ ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ የተሠራው ሥራ ሌሎች እንዲማሩበት አድርጓል:: በኢትዮጵያ የግብርና ሥራን ለማዘመንና የአርሶ አደሩን የእርሻ ሥራ ሙሉ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት አስደናቂ ነው::

ኢትዮጵያ በግብርናው ለውጥን በማምጣት ላይ ትገኛለች:: ይህ ዘርፍ የተሄደበት መንገድ ለተቀረው የአፍሪካ ሀገራት ምሳሌ መሆን የሚችል ነው:: በኢትዮጵያ የተካሄደው ይህ ጉባኤ ሀገሪቱ የደረሰችበትን የእድገት ደረጃ ለተቀሩት አፍሪካ ሀገራት ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነው። ቀሪ ሥራዎችን በተገቢው መንገድ ማስኬድ ከተቻለ ውጤቱ አመርቂ እየሆነ የሚቀጥል ይሆናል::

ግብርና በምግብ እህል ራስን ለመቻል ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚውም ማደግ አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም:: ስንዴን ጨምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ምርትና ምርታማነትን እንዲጨምር እያደረገው ነው:: በኢትዮጵያ ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ትኩረትና ክትትል ዘርፉ ስኬታማ እንዲሆን አስችሎታል:: ስንዴን ጨምሮ በሌሎችም አነስተኛ እርሻ ሥራዎች ላይ የተደረገው ድጋፍ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጎታል:: ይህንን ተሞክሮ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት መውሰድ ይኖርባቸዋል::

በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በስንዴ፣ በሩዝና በሌሎች ምርቶች ላይም ውጤት ማየት ተችሏል። በሀገሪቱ ግብርና ከፍተኛ እመርታ በማምጣት ላይ ነው። ከተናጠል ይልቅ በኩታ ገጠም መሬት እንዲታረስ በማድረግም ምርታማነት ጨምሯል:: የአርሶ አደሩ ኑሮ እንዲሻሻል የተወሰደው ሌላኛው ርምጃ የሚበረታታ ነው:: ኑሮን ከማሻሻል አልፎ ገበያ ተኮር የእርሻ ሥራ ማከናወን ተመራጭ ተደርጓል::

በስንዴ ምርትና ምርታማነት የተመዘገበው ውጤት ግን አሁንም ቀሪ ሥራዎች አሉት:: ዘንድሮ 30 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዷል:: ለዚህም የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ቴክኖሎጂንና ሌሎች ዘመኑን የዋጁ ግብዓቶችን መጠቀም ይገባል:: መሰል እውቅናዎችን በልካቸው በማፍታታትም የበለጠ መሥራት ያስፈልጋል::

ኢትዮጵያ ህልውናዋ ከግብርና ጋር የተቆራኘና ለግብርና እሴት ሰንሰለት ልማት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠች በመሆኗ ዘርፉን በጠንካራ ምርምርና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማገዝ የግድ ይላል:: በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ምርትና ምርታማነትን በዓይነትና በጥራት የሚጨምሩ፣ የአካባቢ ጉዳትን ለመቋቋምና ለመቀነስ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨትና በማቅረብ በዋናነት የግብርናውንና የግብርና ኢንዱስትሪውን አዋጭነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ሀገራዊ ኃላፊነትና ወሳኝ ሚና ያለው ተቋም መሆኑን ተገንዝቦ ይበልጥ ሊተጋ ይገባል::

ኢትዮጵያ ለግብርና የተሰጠ ምቹና ሰፊ ፀጋ ያላት ብትሆንም፣ ይህን ፀጋ በተገቢ ልክ ሳትጠቀምበት ቆይታለች:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን፣ ተስፋ ሰጪ ጥረቶችና ውጤቶች ታይተዋል:: ጥረቶቹ ይበሉ የሚያሰኙ ቢሆኑም፣ ዛሬም ግብርናችንን ከበሬ ቀንበር ለማውረድ ገና ረዥም ርቀት መጓዝ ይቀረናል:: ስለሆነም፣ ዘርፉን ለማዘመን በመስኩ የሚካሄዱ ምርምሮችን ማበረታታት፣ የምርምር ሥራዎች በሰነድ ላይ ብቻ እንዳይቀሩና ወደ ውጤት እንዲቀየሩ በፋይናንስና በቴክኖሎጂ መደገፍ ያስፈልጋል:: አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ በስንዴ የታየውን ምርታማነት በሌሎችም ሰብሎች ለመድገም እንበርታ!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫ የሠራው የፈጠራ ባለሙያ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወጣት ታምሩ ካሳ ይባላል፡፡ ትውልድና እድገቱ አዲስ አበባ ነው፡፡ በኢንዱስትሪያል ኤሌክትሮኒክ የትምህርት ዘርፍ ዲፕሎማውን አግኝቷል፡፡ የፈጠራ ሥራዎች እንደሚሰራ ይናገራል፡፡ ከፈጠራ ሥራዎቹ መካከል አንዱ አትክልትን በዘመናዊ መንገድ ውሃ ማጠጣት የሚያስችለው ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ለእዚህ ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫም ‹‹ስማርት ጋርደንት ወተሪንግ ቴክኖሎጂ›› የሚል ስያሜ ሰጥቶታል፡፡

ወጣት ታምሩ፤ የፈጠራ ሥራ የጀመረው ገና በልጅነቱ ነው፡፡ የፈጠራ ክህሎቱን ተጠቅሞ የሚሰራቸውን የፈጠራ ሥራዎች በየጊዜው እያሳደገ መጥቶ አሁን ብዙ የፈጠራ ሥራዎችና ሃሳቦች እንዲኖሩት ማድረግ እንደቻለም ይገልጻል። ከእነዚህም ውስጥ በሁለቱ የፈጠራ ሥራዎቹ እውቅናና የባለቤትነት መብት አግኝቷል፡፡

እውቅናና የባለቤትነት መብት ካገኘባቸው ሥራዎች መካከል የመጀመሪያ የሠራው በ2010 ዓ.ም የሠራው የአስተያየት መቀበያ ሲስተም /ቄስት ቤዝድ ሰጀሽን / ነው። ይህ የፈጠራ ሥራ ሰዎች አስተያየታቸውን በአስተያየት መስጫ ላይ መጻፍ ሳይጠበቅባቸው በድምጽ /ተናግረው/ አስተያየት መስጠት የሚያስችላቸው ነው፡፡ ማየት የተሳነው ወይም መጻፍ የማይችል ሰው ቴክኖሎጂውን በእጁ ነክቶ አስተያየቱን እንዲሰጥ ያስችለዋል፡፡

ይህ ሲስተም ከኮምፒዩተር ጋር የተያያዘ ነው፤ ለ15ሺ ሰዓት የሚሰጡ አስተያየቶች መዝገቦ መያዝ ይችላል፤ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ በእጅ ስልኩ ላይ የአስተያየቱን መልዕክት በመቀበል ግብረ መልስ መስጠት ያስችለዋል። በተጨማሪም በሁለት መልኩ ተግባቦትን መፍጠር የሚያስችል ሲሆን፤ ለምሳሌ ድሬዳዋ ያለ ሰው አዲስ አበባ ላለው መሥሪያ ቤት አስተያየት መስጠትም የሚችልበት ነው። በተመሳሳይ አዲስ አበባ ያለ ሰው ደግሞ ድሬዳዋ ላለው አስተያየት መስጠት ያስችለዋል፡፡

ሲስተሙ የራሱ የቴሌግራም አድራሻም አለው፤ ሁለት ዓይነት አገልግሎቶችንም ይዟል፡፡ አንደኛው ድምጹ የሚቀርጽበት ሳጥን ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከመሥሪያ ቤት ውጭ ባለበት ቦታ ሆኖ የሚፈልገውን ለመጠየቅና አስተያየት ለመስጠት የሚያስችለው ነው፡፡

ሁለተኛው የፈጠራ ሥራውና የዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምድ ርእሰ ጉዳይ የሆነው ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫ ሲስተም ነው፡፡ ታምሩ ይህን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት መነሻ የሆኑት በተለያዩ ቦታዎች ሲንቀሳቀስ አትክልቶችን ውሃ ለማጠጣት ሥራ ላይ የዋሉት የአትክልት ማጠጫ መንገዶች መሆናቸውን ይገለጻል፡፡

‹‹በትላልቅ መኪናዎች አትክልት ውሃ እንዲጠጣ የሚደርግበት መንገድ ከፍተኛ የውሃ ግፊት መጠን ያለው ነው፤ ይህም ከፍተኛ የውሃ ብክነት ያስከትላል፤ አትክልቶቹ ውሃ ከጠጡ በኋላ የሚፈሰው ውሃ ከአትክልት ሥፍራው አልፎ አስፓልት መንገድ ላይ ሲተኛ እመለከት ነበር፡፡ ተክሎች ሁሉም ተመሳሳይ ባሕሪ ስለሌላቸው መኪናዎች የሚለቁትን ውሃ መሸከም የማይችሉ አሉ፤ የውሃ ግፊት ከፍተኛነት ተክሎቹን እስከ መንቀልና አፈሩንም ጠርጎ እስከ ማንሳት የሚደርስ ችግር ያስከትላል›› ሲል ያብራራል፡፡

‹‹ይህንን ሁሉ ስመለከት የውሃ ግፊቱን ቀንሶ ውሃ ማጠጣት የሚቻልበትን ዘዴ ስለመፍጠር ማሰብ ጀመርኩ፤ ብዙ ሳወጣ ሳወርድ ቆይቼም መፍትሔ ይሆናል ያልኩትን ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫ ሲሰተም መሥራት ቻልኩ›› ይላል፡፡

እሱ እንዳለው፤ የእሱ ፈጠራ የሆነው አዲሱ ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫ ሲሰተም ግን ተክሎቹ ውሃ ሲያስፈልጋቸው እንደየባሕሪያቸው ውሃ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ ሳርና ዛፍ የሚፈልጉት የውሃ መጠን እኩል አይደለም። አዲሱ ሲሰተም አስፈላጊው የውሃ መጠን ለሚፈለገው ተክል እንዲደርስ ማድረግ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ የውሃ፣ የጊዜና የጉልበት ብክነትንም ያስቀራል፡፡

ወጣት ታምሩ እንዳብራራው፤ በዓለም ብዙ ዓይነት የአትክልት አጣጣጥ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚያን ዘዴዎች በሀገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ አይቻልም፤ አሁን ሥራ ላይ ያሉት በከባድ ተሽከርካሪ በመጠቀም አትክልት ውሃ እንዲጠጣ የሚደረግባቸው መንገዶች አማራጭ በማጣት ሥራ ላይ የዋሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ የተሻሉ ቴክኖሎጂዎች በውጭ ሀገሮች እንዳሉ ቢታወቅም ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከፍተኛ በጀት የሚፈልጉ በመሆናቸው ተደራሽ ለማድረግ እጅግ ይከብዳል። በመሆኑም እነዚህ ከውጭ የሚገቡትን ቴክኖሎጂዎች በሀገር ውስጥ በመተካት እዚሁ መሥራት ይቻላል በሚል ሃሳብ ቴክኖሎጂውን እዚሁ መሥራት ተችሏል፡፡

‹‹ይህን ቴክኖሎጂ ከውጭ ከምናስገባ በሀገር ውስጥ ለምን መሥራት አንችልም በሚል በተደጋጋሚ ሙከራዎች በማድረግ እዚሁ መሥራት እንደሚቻል ማሳየት ቻልኩ። የፈጠራ ሥራው አሁን ካለው የከተማዋ ውበትና ከኮሪደር ልማት ጋር ተያይዞ የራሱ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል በመሆኑ እድሉን አግኝቼ ሰርቼ በምችለው ልክ አስተዋጽኦ ማበርከት እፈልጋለሁ›› ሲልም አመልክቷል፡፡

ዘመናዊ የአትክልት ማጠጫ ሲስተሙን በ2010 ዓ.ም መሥራት የጀመረውና በዚያው ዓመትም ከአእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የባለቤትነት መብት እውቅና ያገኘው ወጣት ታምሩ፤ በ2011 ዓ.ም በአንበሳ ግቢ ፊት ለፊት በገንዘብ ሚኒስቴር አጥር ስር ሙከራ አድርጎ ለአንድ ዓመት አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉንም ይገልጻል፡፡



ወጣት ታምሩ እንደሚለው፤ የአረንጓዴ ሥፍራ ውሃ ማጠጫው ከ50 ዓመት በላይ አገልግሎት መስጠት ይችላል። ሲስተሙ በመሬት ውስጥ የሚዘረጋ ነው፡፡ በዚህም አትክልቶችን በአጠቃላይ አረንጓዴ ሥፍራዎችን በቀላሉ ውሃ ማጠጣት ያስችላል፡፡ ሲስተሙ ውሃ ማስተላለፊያ መስመሮች(ታይቶችን) እና የተለያዩ የውሃ አፈሳሰስ ሂደትን መወሰን የሚችሉ ቁሶችን በመጠቀም ይሰራል፡፡ እነዚህ የውሃ አፈሳሰስ ሂደት የሚወስኑት ቁሶች 180 ዲግሪ፣ በ360 ዲግሪ እየተሽከረከሩ በራሳቸው ውሃ የሚያጠጡ ነው፡፡

የመሬቱን ቅርጽ ታሳቢ በማድረግ የአጠጣጥ ሁኔታውን መወሰንም ይቻላል፡፡ እንደየቦታው የአጠጣጥ ቴክኒኩ የተለያየ ሲሆን፣ የኳስ ሜዳዎችና የአስፓልት ግራና ቀኝ ቦታዎች የሚጠጡበት ሂደት ይለያያል፡፡ ለዚህም የተዘጋጁ ከ15 በላይ የውሃ አጠጣጥ ቴክኒኮች አሉት፡፡ እነዚህን ቴክኒኮቹ መጠቀም የውሃ ብክነትን መቀንስ ያስችላሉ። በዚህኛ ቴክኒክ ደግሞ ምንም ዓይነት የውሃ ብክነት አይኖርም፡፡

መስተካከል ያለባቸው ቦታዎች ካሉ ማስተካከል ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ተመሳሳይ ሜትር ካሬ ቦታ ላይ የተለያየ ባሕሪይ ያላቸው ተክሎች ቢኖሩና ልዩነት ቢኖራቸው አንዱ ጋ በማንጠባጠብ ሌላኛው ጋር ደግሞ በከፍተኛ ግፊት ውሃ መጠጣት ካለባቸው እነዚህን ማስተካከል እንደሚቻል ይገልጻል፤ በዚህ ምክንያትም አላስፈላጊ የሆነ ግፊት እንደማይኖር ገልጿል፡፡

የፈጠራ ሥራው ለአትክልቶቹ ያለውን ፋይዳ አብነት ጠቅሶ ሲያብራራም፤ በአዲስ አበባ ከተማ አሁን እየተተከሉ ያሉ ዘንባባዎች ሥራቸው ወደ መሬት በጣም ጠልቆ ስላልገባና ገና ሥር ያልሰደዱ እንደመሆናቸው በከፍተኛ የውሃ ግፊት ሊጎዱ ይችላሉ ሲል ተናግሯል፤ ተክሎቹ አካባቢውን እንዲላመዱ የሚያደርጉ ፈሳሽ ማዳበሪያዎች ከውሃ ጋር ቀላቅሎ ለመስጠት እንዲቻል አትክልቶቹ የሚጠጡበትን ቴክኖሎጂ ከውሃ ቋቱ ጋር በማገናኘነት ቶሎ ስር እንዲይዙ ማድረግ እንደሚቻል ይጠቁማል፡፡

እንደ ታምሩ ገለጻ፤ ዘመናዊ የውሃ ማጠጫ ሲስተሙ መሬት ውስጥ የሚዘረጋ እንደመሆኑ የውሃ ማጠራቀሚያ ቋት /ታንከር/ መሬት ውስጥ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ ሲስተሙ አትክልቶቹ ውሃ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ከማጠራቀሚያው እየቆጠበ ወደ መስመሩ ይልካል፡፡ ውሃ በሌለባቸው ቦታዎች ታንከር እንዲኖር የግድ ስለሚል ልክ እንደ ነዳጅ ታንከሩ መሬት ውስጥ ተቀብሮ በውሃ ይሞላል፡፡

ታንከሩ ውሃ ሲጨርስም በተገጠመለት ሲስተም መሠረት አንድ ሺ ሊትር ውሃ ሲቀረው ውሃ የሚያቀርበው መኪና ውሃ እንዲያመጣለት ለሹፌሩ ወይም ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ውሃ ባለባቸው ቦታዎች ደግሞ ታንከሩ መጠባበቂያ ይይዛል፡፡ ልክ ውሃው እያለቀ ሲመጣ ከዋናው መስመሩ ይሞላል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ከፍተኛ ግፊት በመጠቀም የሚደረግ የውሃ ማጠጣትም ሆነ የትራንስፖርት ምልልስ እንዳይኖር ስለሚያደርግ በብዙ መልኩ ጠቀሜታው የጎላ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ቴክኖሎጂው በተገጠመለት ሲሰተም ዩኒት አማካኝነት በታዘዘው መሠረት ውሃ ያጠጣል፤ ለዚህ የሚሆን የቀንና የሌሊት ጊዜ ማስመረጫ ሲሰተም እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ‹‹እኛ ውሃ እንዲያጠጣልን በምንፈልገው ጊዜና ሰዓት መሠረት በየቀኑ ከስንት እስከ ስንት ሰዓት ማጠጣት እንዳለበት ከሞላን በዚያ መሠረት ትዕዛዙ ይፈጽማል›› ሲል ታምሩ ያብራራል፡፡

በተለይ አትክልቶቹ ውሃን ሌሊት ላይ የሚጠጡ ከሆነ ውሃ በትክክል ስለሚያገኙ ውሃው ለተፈለገለት አላማ እንዲውልና ተኖ እንዳያልቅ ያደርጋል የሚለው ታምሩ፤ ይህ ሲስተም ተግባራዊ ሲደረግ ውሃ ለማጠጣት የሚወጣ ጊዜ እና ጉልበት እንደማይኖርም ተናግሯል፤ ውሃ በማጠጣት ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ሙሉ ጊዜያቸውን ለሌላ የአትክልት እንክብካቤ ሥራ እንዲያውሉ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል ሲል ተናግሯል።



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

**ወጣት ታምሩ ካሳ**

ታምሩ እንደሚለው፤ ሲስተሙን ለመዘርጋት የተለያዩ ሳይቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ውሃ በሌለባቸው ቦታዎች ላይ /ሁሉም ሳይቶች በአንድ ጊዜ ስለማይጨርሱ/ በሁለት መኪናዎች ውሃ መሙላት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ ብዙ ሳይቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን፣ ፊት ለፊት እይታ ላይ የሚውሉ 15 ሳይቶች ግን ያስፈልጋሉ፡፡

ሲስተሙ በአራዳ ክፍለ ከተማ አረንጓዴ ልማት፣ ጽዳትና ውበት አማካኝነት በገንዘብ ሚኒስቴር አካባቢ ባለ መናፈሻ ቦታ መፈተሹን የሚያስታውሰው ታምሩ፣ ቦታው ከሲስተሙ ጋር ሊሄድ የሚችል ሙዚቃ ጭምር እንዲኖረው በማድረግና ሰዎች የሚዝናኑበት እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ እንደነበርም ያስታወሳል፡፡

ይሄኛው ሲስተም ሙዚቃ ብቻ ሳይሆን ሌሎች መልዕክቶች 24 ሰዓት ለማስተላለፍ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነም ይገልጻል። ሲስተሙ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ወደ አካባቢው የሚመጡ ሰዎች ባዩት ነገር ስለመደሰታቸው በየጊዜው አስተያየታቸውን ይገልጹለት እንደነበር ተናግሯል፡፡

እሱ እንዳብራራው፤ የሲስተሙ ሁሉም አካላት በሀገር ውስጥ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ጥገናዎች ቢያስፈልጉ በቀላሉና በፍጥነት ሊጠገን ይችላል፡፡ አብዛኛው መሠረተ ልማቱ መሬት ውስጥ የተቀበረ በመሆኑም የሲስተሙ ደህንነት የተጠበቀ ነው፡፡ ቱቦዎቹ ከፕላስቲክ የተሰሩ መሆናቸውን ጠቁሞ፣ ቶሎ የማይበላሹ በመሆናቸው ለረጅም ጊዜ ያገለግላሉ፡፡

ይህ ሥራ እየተካሄደ ካለው የከተሞች ልማት ጋር ተያይዞ አካባቢን ውብና አረንጓዴ ለማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ‹‹ስማርት ጋርደን ወተሪንግ ቴክኖሎጂ›› መሆኑን አመልክቷል። ስማርት የተባለበት ዋንኛ ምክንያትም መልዕክት ማስተላለፍ በመቻሉና ዘመኑን የሚዋጅ በመሆኑ ነው ብሏል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውብትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የሚመለከታቸው አካላት የፈጠራ ሥራውን መመልከታቸውን አስታውቆ፣ አብረው ለመሥራት ፍላጎት ማሳየታቸውንና እሱም የንድፍ ሃሳብ(ፕሮፖዛል) ማቅረቡን ይገልጻል፡፡

አሁን ሥራ ላይ ያለው ውሃ የማጠጫ መንገድ ቦቴ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጠቁሞ፣ ውሃ የሚያጠጡ አካላት ማጠጣታቸውን ሪፖርት የሚደረጉ ቢሆንም አትክልቱ በትክክል መጠጣትና አለመጠጣቱ በግልጽ አይታወቅም ብሏል፡፡ በአዲሱ ሲሰተም ግን የአረንጓዴ ሥፍራው ውሃ ስለመጠጣትና አለመጠጣቱ ለሚመለከተው አካል በቀላሉ በሚተላለፉ መልዕክቶች አማካይነት እንደሚታወቅ ተናግሯል፡፡

የከተማዋ የአረንጓዴ ልማት ሥራ እየጨመረ ቢሆንም የውሃ እጥረት እያጋጠመ መሆኑ ይስተዋላል የሚለው ታምሩ፣ ይህ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሲሆን ውሃ ከመቆጠብም በላይ ብዙ ቦታዎችን ተደራሽ ማድረግ ያስችላል ብሏል፡፡ ለአንድ ሳይት ምን ያህል ሊትር ውሃ ይበቃል፤ በዚያ አካባቢ ምን ዓይነት እጽዋት አሉ? እጽዋቱ በስንት ደቂቃ ልዩነት መጠጣት አለባቸው የሚሉትን መወሰን እንደሚቻል አስታውቋል፡፡

‹‹የፈጠራ ሥራውን ብቻዬን ብሰራም ከጎኔ ሆነው በሃሳብ እገዛዎችን የሚያደርጉልኝ ግለሰቦች አሉ›› የሚለው ታምሩ፤ ይህንን ሲስተም በትንሹ ሰርቶ ለማሳየት በ150 ሊትር ውሃ በመጠቀም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለመመኮር ማሰቡን ይናገራል፡፡

‹‹አሁን በፈጠራ ከተሰሩት ሥራዎች ያልተሰሩት ይበልጣሉ፤ ገና በጣም ብዙ መሥራት የምንችላቸው ነገሮች አሉ›› የሚለው ታምሩ፣ በአካባቢው ላይ ከሚያያቸውና ከሚያስተውላቸው ችግሮች ተነስቶ ለችግሮች መፍትሔ ማመንጨት የፈጠራ ባለሙያ ሥራ መሆን አለበት ይላል፡፡ ‹‹ወደፊት የማውጣቸው ብዙ ሥራዎች አሉ፤ ባለሙያዎች እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ ብዙ ለሀገር የሚበጁ የፈጠራ ሥራዎች መሥራት ይችላሉ›› ሲል አስታውቋል፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ጉዞ

ክብረአብ በላቸው



የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አምስት ሚሊዮን ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርገውን የኢትዮጵያ ኮደሮች ኢንሼቲቭ በቅርቡ ማስጀመራቸው ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ኢንሼቲቩ ሰልጣኞችን ዘመኑን በዋጀው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል።

የኢትዮጵያ የነገ ተስፋዎች የሆኑ ወጣቶችም ሥልጠናውን በጥሞና በመከታተል ሥራ እና ኩባንያ ፈጣሪ እንዲሁም በዓለም ገበያ ተወዳድረው የሚቀጠሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል ለዚህም ይህንን ትልቅ ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይገባቸዋል ብለዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲጂታል ክህሎት በዲጂታል የታገዘ ማህበረሰብ ለመፍጠር እና አዳዲስ የሥራ እድሎችን ለማመቻቸት ወሳኝ እየሆነ መጥቷል። ነገር ግን ኢትዮጵያ በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ጋር ካሉ ሀገራት ጭምር ስትወዳደር በዲጂታል ክህሎት ወደ ኋላ ቀርታለች።

አዲሱ ትውልድ የዲጂታል ክህሎትን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ካልቻለ ደግሞ እንደ ሀገርም ተወዳዳሪነት አደጋ ላይ ይወድቃል። በመሆኑም ኢትዮጵያ በዲጂታል ክህሎት ያለባትን ክፍተት ለመሙላት የመሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀትና ሁለንተናዊ የዲጂታል ክህሎት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለወጣቶች ተደራሽ ለማድረግ በማቀድ ወደ ሥራ ተገብቷል። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተገቢውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድግ የአምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደርስ ፕሮግራም ተቀርጾ ፋይዳው ከፍተኛ ስለመሆኑ እየተነገረ ነው።

‹‹አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደርስ›› ፕሮግራም በኢትዮጵያ እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግሥታት መካከል በተደረገ ስምምነት የተነደፈ የዲጂታል ክህሎት ሥልጠና መርሃ ግብር ነው። የመርሃ ግብሩ አላማ ወጣቱ ትውልድ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መሳተፍ የሚያስችለውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው።

መርሃ ግብሩ ለሁሉም ተደራሽ የሆኑ የኦንላይን ኮርሶችንና ሌሎች ደጋፊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማቅረብ እ.ኤ.አ በ2026 አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በፕሮግራሚንግ፣ በዳታ ሳይንስ እና አንድሮይድ ልማት መሠረታዊ የዲጂታል ክህሎት ማስታጠቅን ግብ ያደረገም ነው።

በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ስዩም መንገሻ እንደሚናገሩት፤ በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ላይ ከተቀመጠው ዋና ነገር አንዱ የዲጂታል ውስንነት መሙላት ነው። ለዚህ ደግሞ ብዙ ቁጥር የሚያሳትፍ እንደ ኢትዮጵያን ኮደርስ አይነት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው።

በዚህ ፕሮግራም የሚሰጡ ኮርሶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው የሚሉት አቶ ስዩም፤ የሚሰጡ ኮርሶች መሠረታዊ ናቸው ማለትም ዳታ ሳይንስ፣ ፕሮግራሚንግ፣ አንድሮይድ ፕሮግራሚንግ ላይ የኢትዮጵያ ኮደርስ ፕሮግራም በዋናነት ይሰጣሉ እነዚህ ኮርሶች አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጠቃሚነታቸው ከፍተኛ ነው ይላሉ።

የሥልጠናዎቹ ይዘቶች የሚቀርቡት ዓለም አቀፍ የዲጂታል ክህሎቶችን በኦንላይን (በማስተማር ስመጥር ከሆነው ከዩዳሲቲ ፕላትፎርም ጋር በመተባበር ስለመሆኑ የሚናገሩት አቶ ስዩም፤ ፕላትፎርሙ የተለያዩ የፕሮግራሚንግ የዌብ ልማትን እና ሌሎች በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የኮዲንግ ሥልጠናዎችን እንደምሰጥ ይናገራሉ። በፕላትፎርሙ የሚሰጡት ኮርሶች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው እና ከኢንዱስትሪውም ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው። ለመነሻም ሥልጠናዎቹ በአራት የሥልጠና ዘርፎች ላይ የሚሰጥ ሲሆን፤ ሰልጣኞች በተዘጋጀው በፕላትፎርም በመመዝገብ ኮርሶቹን በኦንላይን የሚወስዱ ይሆናል።

እንደ አቶ ስዩም ገለፃ፤ አንዱ ኮርስ እስከ ስድስት ሳምንት ሊወስድ ይችላል። በኦንላይን ለየኮርሶቹ አማካሪዎችና ውይይት የሚያደርግ የኦንላይን ማህበረሰብም ይኖራል። አሁን ለመነሻ ከቀረቡት የስልጠና ይዘቶች በተጨማሪ በቀጣይ ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረጉ ተጨማሪ ይዘቶች የሚካተቱ ይሆናል።

እነዚህን ኮርሶች ማንኛውም ሰው መውሰድ አለበት የግድ የኮምፒውተር ባለሙያ መሆን አይጠበቅም የሚሉት አቶ ስዩም፤ የኮርስ አሰጣጡም ቀለልና ለየት ያለ ነው በቪዲዮና በጽሑፍ የሚሰጠውን ትምህርት በማዳመጥና በማንበብ የሚሰጡ ጥያቄዎችን በመመለስ ብቁ የመሆን ዕድል የሚሰጥ ነው ነገር ግን ዝም ብሎ ብቁ የመሆን ዕድል የለም ሰርተፍኬት ለማግኘት ከሚሰጡ ጥያቄዎች 60 በመቶ የሚሆኑትን መመለስ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ሥልጠናውን በገንዘብ መውሰድ ቢፈለግ ክፍያው በዶላር ስለመሆኑ የሚናገሩት አቶ ስዩም፤ ይህ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው ነገር ግን ለኢትዮጵያውያን በነፃ ቀርቧል ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በቤታቸው ሆነው በፈለጉት ሰዓት ኮርሱን መውሰድ ይችላሉ ይህ በቀላሉ የማይገኝ ዕድል በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም ይገባል ይላሉ።

በአሁኑ ወቅት ከ259 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሥልጠናውን እየወሰዱ እንዳለ የሚነገሩት አቶ ስዩም፤ ከእነዚህ ውስጥ ከ35 ሺህ በላይ ሰልጣኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መውሰዳቸውን ተናግረዋል። ይህንን ፕሮግራም በበላይነት የሚያስተባብር ተቋም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሠራተኞች ጭምር በፕላትፎርሙ የሚሰጡ ኮርሶችን ተከታትለው ብቁ እንዲሆን እየተሰራ ስለመሆኑ የሚገልፁት አቶ ስዩም፤ ሌሎችም የፌዴራል ተቋማት ሠራተኞቻቸው የዲጂታል ዓለሙን ተገንዝበውና በቂ እውቀት ኖሯቸው ሥራዎችን መሥራት እንዲችሉ ይህንን ሥልጠና እንዲወስዱ መበረታታት እንደሚገባቸው ይናገራሉ።

በዚህ ፕሮግራም ሰልጥነው ብቁ የሆኑ ሰዎች ባሉበት ሆነው ተጨማሪ ሥራ መሥራት እንደሚችሉ የሚናገሩት አቶ ስዩም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ አውሮፓ ላይ ላለ ድርጅት ሥራ መሥራት ይቻላል ይህ በአንድ የገቢ ምንጭ ብቻ ጥገኛ የሆነ ኑሮ ያለውን ሰው ሕይወቱን መለወጥ የሚችልበት አጋጣሚ የሚፈጥር ነው ይላሉ።

የሥልጠና ፕሮግራሙ በመላው ሀገሪቱ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑ የሚናገሩት አቶ ስዩም፤ የሁሉም ክልል ፕሬዚዳንቶች ኃላፊነት ወስደው የሚመሩት ይህንን የሥልጠና ፕሮግራም አፈፃፀም የሚከታተል ኮሚቴ አለ ይህ ኮሚቴ የሥልጠና ሂደቱን ውጤታማነት ይገመግማል፣ ችግሮች ካሉ እነርሱን በመለየትና እንዲፈቱ በማድረግ ፕሮግራሙ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ተናግረዋል።

የኢንተርኔት መሠረተ ልማት ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች የሚገኙና ይህንን ሥልጠና መውሰድ የሚፈልጉ ሰዎች በአቅራቢያቸው በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመሄድ ሥልጠናውን መከታተል እንዲችሉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር መግባባት ላይ ስለመደረሱ ተናግረዋል።

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የመንግሥት አገልግሎቶች ዲጂታል እንዲሆኑ ግብ ተቀምጦ እየተሠራ እንዳለ የሚናገሩት አቶ ስዩም፤ አገልግሎት አሰጣጡ ዲጂታል ሆኖ ህብረተሰቡ መጠቀም ካልቻለ ጥቅም የለውም ለዚህ ደግሞ እንደ ሀገር የዲጂታል ክህሎት ያስፈልጋል አገልገሎት ሰጪና ፈላጊ አካላት በቂ የቴክኖሎጂ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ አኳያ በዚህ ሥልጠና በንቃት መሳተፍ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

የቴክኖሎጂ ባለሙያና የፋርስ ቴክኖሎጂ ኩባንያ መሥራች ወጣት ኤልያስ ይርዳው በበኩሉ እንደሚናገረው፤ ዓለም ከዲጂታላይዜሽን አልፎ ወደ ሰው ሠራሽ የቴክኖሎጂ ምርምር ተሸጋግሯል ከዚህ አኳያ ነገሮችን መረዳት የሚችሉ ከተረዱ በኋላ ደግሞ የመፍትሔ ሃሳብ ማምጣት የሚችሉ ወጣቶችን ለማፍራት ይህ የኢትዮጵያን ኮደርስ ፕሮግራም ከፍተኛ አበርክቶ እንደሚኖረው ይናገራል።

ከዚህ በፊት በፋርስ ቴክኖሎጂ አማካኝነት መሰል የቴክኖሎጂ ሥልጠና የወሰዱ ወጣቶች በአሁኑ ወቅት በሀገራቸው ውስጥ ሆነው አውሮፓና አሜሪካ ለሚገኙ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩ እንዳለ የሚናገረው ወጣት ኤልያስ፤ ይህ የኢትዮጵያን ኮደርስ ፕሮግራምም ሰፊ ቁጥር ያላቸውን ወጣቶች ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ተናግሯል።

በቀጣይ ሥራ በመሥራት እራሴን፣ ቤተሰቤንና ሀገሬን መጥቀም እፈልጋለሁ የሚል ማንኛውም ሰው በእንደዚህ ዓይነት የቴክኖሎጂ ሥልጠናዎች እራሱን ማብቃት ግዴታ ይኖርበታል የሚለው ወጣት ኤልያስ፤ በተለይ ወጣቶች ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ራሳቸውን ለመለወጥ መዘጋጀት እንዳለባቸው ይናገራል።

በአሁኑ ወቅት ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ከሚያስገባው ዶላር በላይ በቴክኖሎጂ ልማት የተሰማሩ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ እያስገቡ ነው የሚለው ኤልያስ፤ አሁን ያለነው እውቀት ገንዘብ የሆነበት ዘመን ላይ ነው ከዚህ አኳያ ይበልጥ እንደ ሀገር ተጠቃሚ ለመሆን በዚህ ዓይነት ሥልጠና የበቁ ወጣቶች እንደሚያስፈልጉ ይናገራል። ለአብነት ህንድ ከሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርቷ ከ230 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የበቁ ወጣቶች የትም ሳይሄዱ ባሉበት ሆነው ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሚሰሩት ሥራ አማካኝነት እንደምታገኝ ተናግሯል

በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጥናት መሠረት ይህ ዘርፍ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚያመነጨው ገቢ ወደ አምስት ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል ከዚህ አኳያ ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን መዘጋጀት እንደሚገባ ያስረዳል። በሀገር ውስጥም በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ስለመምጣቱ የሚናገረው ኤልያስ፤ እነዚህ ድርጅቶች የግድ ብቁ የቴክኖሎጂ እውቀትና መረዳት ያላቸውን ወጣቶች ይፈልጋሉ ስለዚህ ወደፊት ለሚጠብቀው ዕድል ከአሁኑ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል ይላል።

መንግሥት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቀውን ይህን ዓይነት የሥልጠና ዕድል በነፃ ማቅረቡ የሚያስመሰግነው ነው የሚለው ኤልያስ፤ በተለይ ከሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ወጣት በመሆኑ ይህንን ሰፊ ቁጥር ያለው ወጣት ተደራሽ ለማድረግ በየዓመቱ የሚቀጥል ፕሮግራም መሆን አለበት ይላል።

ይህ የኮደር ፕሮግራም ኢትዮጵያ ለማሳካት ያቀደችውን ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ውጥን ከግብ ለማድረስና በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሰው ከፍተኛ ገቢ ተከፋይ ለመሆን ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ይናገራል።

ወጣት ኤልያስ እንደሚያስረዳው፤ በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ሁሉም ቴክኖሎጂ እየታጠቀ ነው ቴክኖሎጂ በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርና ዘርፍ ተግባራዊ እየሆነ ነው። ይህንን ቴክኖሎጂ ደግሞ ተረድቶ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ በቂ እውቀት ሊኖር ይገባል ከዚህ አንፃር መዘጋጀት ለነገ የማይባል ነው።

በአጠቃላይ አስተያየት ሰጪዎቹ እንደተናገሩት፤ የሀገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ በወጣቶች እጅ በመሆኑ የነገዋን ኢትዮጵያ የሚቀርፁት የፈጠራ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች እነዚህ ወጣቶች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮ ኮደርስ ፕሮግራም ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በዲጂታል ሥነ ምህዳሩ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ክህሎትና እውቀት በማስታጠቅ አዳዲስ እድሎች እንዲፈጠርላቸው እና ሀገሪቱ በቴክኖሎጂው መስክ ወደፊት እንድትገሰግስ በር የሚከፍት በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም ይገባል፡፡

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ቅመማ ቅመምን ከማጣፈጫነት ባሻገር

## - በባለርዕይዋ ወይዘሮ

**አመለወርቅ ከበደ**

አንድ ሰው ከገጠር ወደ ከተማ እንጂ፤ ከከተማ ወደ ገጠር ሄዶ ለመኖር ሆነ ለመሥራት ሲያስብ ብዙም የተለመደ አይደለም:: በተለይ ደግሞ ብዙ መሠረተ ልማቶች ወደ አልተሟሉባቸው እንደ የሀገሪቱ ገጠራማ ክፍል ሲሆን፣ ነገሩ ከባድ ይሆናል:: ነገር ግን ራሄል ሕሩይ፣ የገጠሩን የተፈጥሮ ስጦታ እንጂ የመሠረተ ልማቱን ጉድለት አልተመለከተችም::

ምንም እንኳን ትውልድና እድገቷ ለአፍሪካም ለኢትዮጵያም መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ቢሆንም፤ የሰነቀችው ራዕይ ወደ ገጠር እንድትመለከት አደረጋት:: ራዕይዋን ለመከተል በመወሰኗም ለበርካታ እናቶች በጓሯቸው ሰርተው የሚለወጡበትን እድል ልትፈጠር ችላለች::

ለካፋ እና ቤንቺ ሻኮ አካባቢዎች አዲስ የሥራ ባሕልን በመፍጠር አምስት ሺህ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በር ከፋች ናት:: እስካሁን በሠራቸው ሥራም ከሀገር ውስጥ አልፋ በአፍሪካ ደረጃ ተሸላሚ ከመሆን የዘለለ በተለያዩ የሥራ ውድድሮች ዳኛ በመሆን፤ በአንዳንድ መንግሥታዊ ተቋማት ዓመታዊ እቅድ ዝግጅት ላይ በማማከር ለመሳተፍ ችላለች::

ወይዘሮ ራሄል፣ የዳማሴን እሴንሻል አይል ድርጅት መሥራችና ኃላፊ ስትሆን፣ ድርጅቷ የሚሰራው በካፋ እና ቤንቺ ሻኮ ዞኖች፤ እናቶች እና ወጣቶች በጓሯቸው የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች እንዲያመርቱ የተለያዩ ከዘር አንስቶ በሌሎች ነገሮች ይረዳል:: ምርቱ ከተመረተ በኋላ መልሶ ከአርሶ አደሮቹ በመግዛት ለገበያ የማቅረብ ሥራ ይሠራል::

የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የተማረችው በአዲስ አበባ ከተማ ሕይወት ብርሃን ትምህርት ቤት ነው:: የከፍተኛ ትምህርቷን በፋርማሲ የሙያ ዘርፍ ተምራ ከፍተኛ ባለሙያ እስከመሆን ድረስ ሠርታለች:: አሁን እየሠራች ባለችው የቅመማቅመም እና የግብርና ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን መንገድ እንዲሆናት በተለያዩ ጊዜያት ስልጠና ከመውሰድ ያለፈ "በአግሪ ቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን" ሁለተኛ ዲግሪዋን ተምራለች::

ትዳር መስርታ ሶስት ልጆችን ያፈራች ሲሆን፣ ባለቤቷ በሞት ስለተለያት ልጆቹን የማሳደግ ኃላፊነት በእርሷ ላይ ሊወድቅ ችሏል:: ከልጆቿ በተጨማሪ እናቷን፣ አክስቷን እና የአክስቷን ልጆች የምታስተዳድረው እርሷ ናት። ልጆቿ እና ቤተሰቦቿ የሚኖሩት አዲስ አበባ ስለሆነ፤ አብዛኛው ጊዜ በሥራ ምክንያት ለረጅም ጊዜያት ክልል ከተሞች ስለምትቆይ ላይገናኙ የሚችሉበት አጋጣሚ መኖሩን ትገልጻለች::

ወይዘሮ ራሄል፣ ወደ ቅመማ ቅመም ልማት ሥራ የገባችው፤ ከባሕላዊ መድኃኒቶች እና የውበት መጠበቂያዎች ጋር ተያይዞ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሔ አካል ለመሆን በማሰብ ነበር:: "የባሕላዊ መድኃኒቶቻችን ብዙ ጊዜ በዘልማድ ይደረጋሉ እንጂ በሥነ ሥርዓት አላስቀመጥናቸውም፤ ለሌላው ዓለም እንዲደርሱ አልሠራንባቸውም::" ስትል ትናገራለች::

እያደገች ስትመጣ የባሕላዊ መድኃኒቶች በስም ደረጃ ብቻ የምንጠቀማቸው ብቻ ሳይሆን፤ በስፋት ተመርቶ ለዓለም ቢሰጥና ቢለማመደው የሚል እሳቤ አደረባት:: ከፍ እያለች ስትመጣ ባሕላዊ የውበት መጠበቂያዎች ላይ መሥራት የበለጠ ፍላጎቷ እየሆነ ስለመጣ አቅጣጫዋን ወደዚህ ዘርፍ አዞረች:: ይህ ፍላጎቷ የመመረቂያ ጽሑፏን በውበት መጠበቂያ ዙሪያ እንድትሰራ ተጽእኖ ያሳደረባት እንደሆነም ታመለክታለች::

ወይዘሮ ራሄል፣ የመመረቂያ ጽሑፏን የሰራችው በወይባ ጢስ ላይ ነው:: ወይባ ከውበት መጠበቂያነት ያለፈ፤ ለጤና ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ፤ 12 ዓይነት ዝርያ ስላለው እሱን አምርቶ በመሸጥ በኢኮኖሚ ረገድም ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ትናገራለች::

"እነዚህን ነገሮች በሥነ ውበት መጠበቂያዎች ምርምር ላይ ለመሥራት ቀድሜ ባስብም፤ ምርምር ላይ መሥራት ብር እና እውቅና ስለሚፈልግ ጊዜ የሚፈጅ ነው። ስለዚህ መዓዛማ ዘይቶች የሚባሉ በባሕር ዛፍ፣ በጠጅ ሳር የሚሰሩ ስላሉ እነሱን ለማምረት አሰብኩ። ከእነሱም ጋር ተያይዞ የተለያዩ የውበት መጠበቂያዎች ለማምረት ስነሳ ጥሬ እቃ አጠረኝ::" ትላለች::


ፎቶ፡- በሪሁን ታደሰ

ወይዘሮ ራሄል ሕሩይ

**በምርምር እና የማህበረሰቡን ባሕላዊ እውቀት ተጠቅማ የምታገኛቸውን የቅመማ ቅመም ዝርያዎች በሰፊው በተመሳሳይ ደረጃ እንዲኖሩ ለማድረግ ችግኝ ጣቢያዎችን አቋቁማ ዝርያዎች ላይ ትሰራለች**

ዳማሴን ድርጅት በ2006 ዓ.ም የውበት መጠበቂያዎችን ማምረት አላማው አድርጎ ቢመሰረትም በጥሬ እቃ እጥረት ምክንያት፤ የውበት መጠበቂያ ጥሬ እቃዎችን በቋሚነት ለገበያ ለማቅረብ ነው ወደ ግብርናው ዘርፍ ሊገባ የቻለው::

"ቡና ላይ ልሠራ ብዬ ብመጣ እንደ ሀገር ከዚህ በፊት የተሰራ ነገር ስላለ አልቸገርም:: የተለያዩ ቡና አቅራቢ ማህበሮች ስላሉ ከእነሱ ጋር ልሠራ እችላለሁ:: ነገር ግን ቅመማ ቅመም ላይ የተሰራ ነገር ባለመኖሩ የተስተካከለ ነገር ስላልነበረ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥሬ እቃ አቅራቢዎቹን በማፈላለግ ረገድ አደራጅቶ የመሥራቱ ነገር የኔ ሆነ:: "ስትል ትናገራለች::

ከግብርና ምርምር ጋር መሥራት ብትጀምርም፤ ግብዓቶቹን ማግኘት ቀጣይነት ያለው እና ቋሚ ጥያቄ እንደመሆኑ፤ አምርቶ ጥሬ እቃ የሚያቀርብላትን ወደማፈላለግ ገባች:: ካፋና አካባቢው ሄዳ ለመሥራት ምክንያት የሆናት በብዝሀ ሕይወት የሚሰራ ድርጅት በአካባቢው ያሉ ደኖች የአካባቢውን ነዋሪ ተጠቃሚ እንዲያደርግ እና ቀጣይነት እንዲኖረው ፕሮጀክት ይዞ ነበረና፤ እርሷ ጥሬ እቃ አቅራቢ ስለምትፈልግ ፕሮጀክቱን እንደትይዝ ተደረገ::

ነገር ግን አብዛኞቹ ምርቶች ከጫካ የወጡ ባለመሆናቸው አመቺ አልነበረም:: ምክንያቱም ጥራታቸው ተመሳሳይ አይደለም:: ጫካ ውስጥ ያለ ነገር የሕዝብ ከመሆኑ አልፎ የእንስሳት እና የዱር እንስሳቱም ፍላጎት አለው:: ሌላው ነገር በቀጣይነት ለማቅረብም ብዛት የለውም::

"ስለዚህ የራሴን መሬት ወስጄ ላልማ የሚለውን ሃሳብ ሳስብ ተቀባይነት ማግኘቱ ትንሽ ስለሚከብድ፤ ማህበረሰብ ውስጥ ስመለከት በጉልህ ያዩት ትርፍ ነገር መሬት ነው:: እንደ ከተማ ልጅ አንድ ሺህ ካሬ እንጂ አንድ፣ ግማሽ እና እስከ 10 ሄክታር ድረስ ጓሮ ያለው ሰው አይቼ አላውቀወም:: እነዚህ መሬቶች ቢገጣጠሙ ትልቅ መሬት ይወጣቸዋል፤ ሰዎቹንም ወደ ሥራ ማሳተፍ ይቻላል የሚል ሃሳብ ላይ ደረስኩ::" ስትል ትናገራለች::

"እነሱ በዚህ ሁኔታ ከሰሩ ደግሞ ለእኔ አቅራቢ ስለሚሆኑኝ እኔው በራሴ አቅራቢ ፈጠርኩ ማለት ነው:: ሰዎቹ ዘንድ ምንድነው የሚጎድለው የሚለውን ስመለከት እውቀት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና በማህበር መደራጀት ያሉ ክፍተቶች መሆናቸውን ተመለከትኩ:: ሥራውን ለመሥራት ደግሞ በማህበር ተደራጅተው በተቋም ደረጃ ማቋቋም ያስፈልጋል:: ስለዚህ ከመንግሥት እና ሊያግዙኝ ከሚችሉ አካላት ጋር ደረጃ በደረጃ እያናገርኳቸው ለመሥራት ቻልኩ::" ትላለች::

ወደ ሥራው ስትገባ የነበሩትን 20 አርሶ አደሮች ብቻ ማሳተፍ የቻለች ቢሆንም፤ አሁን ካፋ ዞን ላይ አምስት ሺህ ሴት አርሶ አደሮች በማሳተፍ እየሠራች ነው:: ከዚያም ባለፈ በአንድ ዞን ብቻ ሳትገደብ ወደ ቤንቺ ሻኮ ዞን ተሻግራ እየሰራች ትገኛለች:: የሥራ ቦታዋን ከማስፋፋት እና የተሳታፊ አምራቾችን ቁጥር ከመጨመር በተጨማሪ ምርቶቹ የሚቀርቡበት ትላልቅ ገበያዎችን በማፈላለግ ረገድም እየሰራች ነው::

የቅመማ ቅመም ምርቶቹን በሥርዓት አምርቶ ለዓለም የማስተዋወቅ ተግባር በተወሰነ መልኩ የተሳካላት ይመስላል:: አሁን ላይ ለሁለት ሀገራት በተወሰነ መልኩ የቅመም ምርቶቹን እያቀረበች ይገኛል:: በቀጣይ ምርቶቿን በስፋት እያመረተች ባልተቋረጠ መልኩ ለተለያዩ ሀገራት ለመላክ፣ ምርት መጨመር ላይ እና ገበያ የማፈላለግ ሥራ ላይ እየሠራች እንደሆነ ትናገራለች::

"ከሴቶች ጋር እንድሠራ ያደረገኝ ምክንያት ካፋ ዞን ስመጣ፤ የራሴን የእርሻ መሬት ማግኘት ባለመቻሌ እንደ አማራጭ የወሰድኩት የሌሎቹን የእርሻ መሬት መጠቀም ነው:: ወንዶቹን ሳናግር ሥራው ገና ሙከራ ላይ ስለነበር እምነት ኖሯቸው ከዚህ በፊት የለመዱትን የሰብል ዓይነት ትተው ከኔ ጋር ቅመማ ቅመም ላይ በጋራ ለመሥራት ባለመፈለጋቸው ሌላ አማራጭ ስመለከት ሰፋፊ ጓሮ እንዳለ አስተዋልኩ:: ጓሮውን ደግሞ የሚያስተዳድሩት ሴቶች ናቸው::" ትላለች::

"ለምሳሌ ለ10 ሴቶች ግማሽ ሄክታር መሬት ቢኖራቸው ስንደምረው አምስት ሄክታር ይሆናል። በዚህ ሁኔታ በርካታ ሴቶች በተሳተፉ ቁጥር ሄክታሩ እየጨመረ ይመጣል:: ሴቶቹም እዛው ቤታቸውን እና ልጆቻቸውን እየተንከባከቡ በጓሯቸው በመሥራት ገንዘብ ከሚያስገኘው ሥራ ላይ ሌላ መሳተፍ ተጨማሪ እድል ሆነ ማለት ነው::" ስትል ታስረዳለች::

ምንም እንኳን የተመረተውን ምርት መልሳ ከአርሶ አደሮቹ ገዝታ የምትረከብ ቢሆንም፤ አርሶ አደሮቹን ከማደራጀት አንስታ፣ ከዘር መረጣ እስከ ችግኝ ማቅረብ እና ወደ እርሻ ገብታ አተካከሉን እስከ ማሳየት ድረስ ትሰራለች:: በዚህ ካምፓኒው የግል ይሁን፣ ግብረሰናይ ድርጅት ይሁን፣ የመንግሥት ይሁን ለብዙ ሰው ግራ ያጋባል ትላለች::

በአሁኑ ወቅት ከሁለት ሺህ ሄክታር መሬት በላይ የደረሰች ሲሆን፣ በካፋ ዞን በአምስት ወረዳዎች በቤንች ሻኮ ዞን ሁለት ወረዳዎች ላይ እየሠራች ነው:: ቅመማ ቅመም ተያያዥነት ያለው እንደ መሆኑ 15 ዓይነት ቅመሞችን ነው እያመረተች ያለችው::

"ሽሮ እንኳን ብንወስድ የሚፈጨው ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል ፣ ኮረሪማ ፣ ነጫ አዝሙድ እና ሌሎች ቅመሞች ገብተውበት ነው:: ስለዚህ ቅመም አንድ ሰብል ብቻ ስላልሆነ አንዱ ቅመም ካንዱ ጋር አብሮ መሆን ስላለበት የተለያዩ ዓይነት ቅመሞችን ነው የምናመርተው። ለዚህ ደግሞ የታወቁ ዝርያዎች ከምርምር ተቋማት መምጣት ይኖርባቸዋል:: በዚህ ረገድም የምርምር ተቋማት ቋሚ አጋሮቼ ናቸው::" ትላለች::

እናቶች የራሳቸው የሆነ ባሕላዊ እውቀት አላቸው የምትለው ወይዘሮ ራሄል፤" ካፋ ላይ ይሄን እውቀታቸውን ለመጠቀም እናቶችን ከየቀበሌው ሰብስበን ለቅመምነት ከሚሆኑ የቅጠል ዝርያዎች የትኛው ይሻላል ብለን አስመረጥናቸዋል ትላለች:: እነርሱ የመረጡትን ደግሞ አባዝተን አምጥተን መርጠው ወስደው እንዲተክሉ አድርገናል:: አሁን ካፋ አብዛኛዎቹ ሴቶች ጓሮ ሮዝመሪ፣ ኮሰረት፣ ዝንጅብል እና ሎሚናታ አለ::" ስትል ትገልጻለች

በምርምር እና የማህበረሰቡን ባሕላዊ እውቀት ተጠቅማ የምታገኛቸውን የቅመማ ቅመም ዝርያዎች በሰፊው በተመሳሳይ ደረጃ እንዲኖሩ ለማድረግ ችግኝ ጣቢያዎችን አቋቁማ ዝርያዎች ላይ ትሰራለች:: እስካሁን ወደ ስድስት የሚደርሱ የችግኝ ጣቢያዎች አቋቁማለች::

"አሁን ሴቶቹም ሥራውን ስለለመዱ ችግኝ ሲያፈሉ አንዳቸው ለአንዳቸው ያከፋፍላሉ:: መንግሥት በሚገርም ሁኔታ ከእኛ ገዝቶ ያከፋፍላል:: ከዚህ በፊት የአካባቢው ኮሮሪማ ተወዳጅ አልነበረም:: በዝርያ ረገድ በሠራነው ሥራ አሁን ላይ 'እስፔሻሊቲ' ተብሎ መሸጥ ጀምሯል::" ትላለች::

ወይዘሮ ራሄል፣ የከተማው ድምቀት ሳይጎትታት የሄደችለት ዓላማ በጊዜ ሂደት አብቦ ከራሷ አልፋ ለሌሎች እንድትደርስ አድርጓታል:: በዚህም እስካሁን ባሰየችው የሥራ ውጤት በአህጉር ደረጃ በውጤታማ ገበሬ ሴቶች ዘርፍ ተሸላሚ የሆነች ሲሆን፣ እንደ ሀገር ሥራ ፈጣሪ ተብላ ለመሸለም በቅታለች::

በሌላ በኩል ደግሞ እስካሁን ባሳለፈችው መንገድ ተመስርታ አማካሪ እና ዳኛ ሆና ለመሥራት ተመራጭ ሆና በመገኘቷ እድሉን ማግኘት ችላለች:: ሁለት ጊዜ በሥራ ፈጠራ ውድድሮች ላይ በዳኝነት ተሳትፋለች። ከዚህ በተጨማሪ ቡና እና ሻይ ባለሥልጣን ዓመታዊ እቅድ ሲያዘጋጅ በቅመማ ቅመም ዘርፍ እስከ ማማከር ደርሳለች::

ቀጣይ እቅዷ ደንበኞች በሚፈልጉት መልኩ ለበርካታ ሀገራት የቅመማ ቅመም ምርቶችን ማቅረብ እና በዘርፉ ምርምሮችን ወደ ማድረግ መዛወር መሆኑን የምትገልጸው ወይዘሮ ራሄል፣ በመጨረሻም የገንዘብ ተቋማት ብድር በማመቻቸት ረገድ ትብብር ቢያደርጉ ስትል ጥሪዋን አቅርባለች::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ውድድር በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ከታህሳስ 3 ቀን 1980 ዓ.ም ጀምሮ ለ15 ቀናት እዚህ አዲስ አበባ እና አስመራ በተካሄደበት ወቅት የነበረው የሕዝብ ስሜት ከጣራ በላይ ሆኖ ያለፈ መሆኑ በወቅቱ በሰፊው ተዘግቧል።

በሁለት ምድብ ተከፍሎ በስድስት ቡድኖች መካከል ሲካሄድ በነበረው፤ የዓለምን ዓይንና ጆሮ ቀስፎ በመያዝ እስካሁን አቻ ያልተገኘለት ውድድር ሲካሄድ በነበረበት ወቅት ዜጎች ይህንን ሀገራዊና ብሄራዊ ስሜታቸውን በተለያዩ ሚዲያዎች ሲገልፁ የነበረ ሲሆን፤ አንዱና ዋንኛው ደግሞ በዚህ ጋዜጣ ላይ ሲፃፉ የነበሩት ግጥሞች ናቸው።

ባለፈው ሳምንት በጨዋታው ፍፃሜ የኢትዮጵያ እና የዚምባቡዌ ብሄራዊ ቡድኖች ለዋንጫ በሚፋለሙበት (ታህሳስ 22) ወቅት ከፍልሚያው በፊት፤ በዋዜማው፣ ዋንጫውን ከማግኘታችን አስቀድሞ ልናገኝ እንደሚገባ በመተንበይ፣ "የእኛ ይሁን!" በሚል ርእስ የተገጠሙ ስንኞችን ማቅረባችን ይታወሰል። ዛሬ ደግሞ ተንባይ ግጥሞቹ ተሳክቶላቸው ዋንጫውን ካገኘን በኋላ የተቋጠሩ ስንኞችን ይዘን ቀርበናል። እነዚህን ግጥሞች ከሌላው ለየት የሚያደረጋቸው ለድል ያበቁንን ተጫዋቾች ለታሪክ ምስክርነት ይበቁ፤ ውለታቸው አይረሳ፤ ድላቸው ይዘከር ዘንድ በውስጣቸው በዝርዝር መያዛቸው ነው። እኛም፣ የታሪክ አካል ነንና ይህንኑ ታሪክ ለአሁኑ ትውልድ ማስተላለፉ ላይ ልንሠራ የሚገባ መሆኑ ላይ በማመን፣ ያንን በወርቅ የተፃፈ የሀገራችንን የእግር ኳስ ታሪክ ለትውልድ ልናሻግረው ወደድን።

ብሄራዊ ቡድናችን ለዋንጫ ሽሚያ የደረሰው ከአዲስ አበባ ምድብ ከታንዛኒያና ከዛንዚባር ጋር 1 ለ 1 ተለያይቶ፤ ኬንያን 2 ለ 1 አሸንፎ፤ የምድቡን ማጣሪያ በሁለተኛነት ካለፈ በኋላ በአስመራ ምድብ አንደኛ ሆኖ ያለፈውን ዩጋንዳን 3ለ0 በሆነ ውጤት አሸንፎ መሆኑ በወቅቱ ተዘግቦ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

ኢትዮጵያ ይህንን የምስራቅና የመካከለኛው አፍሪካ) ሴካፋ) ጨዋታ ስታዘጋጅ ይህ የመጀመሪያዋ መሆኑ፤ ብሄራዊ ቡድናችንም ለዋንጫ ሽሚያ ሲደርስና ይህንን ዋንጫ ሲያገኝም የመጀመሪያው መሆኑ በዚያው ወቅት ሰፋ ያለ የሚዲያ ሽፋን ያገኙ ዘገባዎች ነበሩ።

በተረፈ ትዝታውን ለአንባቢያን ግጥሞቹን ወደ ማስታወስ እንሂድ።

### የቅኔ ስጦታ ስባስውስታ

የዝምባቡዌ አጥቂዎች ግብ እያንዣበበ
የጥቃት ግድግዳው በራችን ተካበ።
ወገኖችህ ሁሉ ድል እንደ ጠማቸው፤
አደባባይ ወጥተው ሲቃ ሲይዛቸው፤
ልበሙሉ ጀግና አንተነህ ዳኛቸው።
በገና ዋዜማ በገና ጨዋታ፤
አሲላዬ ሲሉ እነሙሉጌታ፤
ሜዳውን በሙሉ አየነው ቃኘነው፤
ዓይናችን ልባችን ካማኑኤል ጋር ነው።
ደገስገስ እያለ ሲጨነቅ ወገኔ፤
ጨለማ ገፋፊው በቀለ ብርሃኔ።
23 ዓመታት እንደማያልፍ የለም
ገና አሁን ዘንድሮ ሆነልን ሙሉአለም።
ጥቃት የማይወደው ወገንህ በሙሉ፤
ገብረመድህን ኃይሌ ይሉሀል አምበሉ።
አቦ ዝም በሉ ደስ ብሎናል እኛ!
መንግሥቱና ነጋሽ ጌቱና ሰለሞን የኛ አስራት አዱኛ።
ሀቁን እንመስክር ባህላችን ነውና፤
በኳስም ታጋይ ነው የዚምባቡዌ ጀግና!
ትናንትም እነመንጌን እንዴት ተሰማቸው!
ይድነቃቸውንስ መሬት ቀለላቸው!
(አበባው ይግዛው)

### እንኳን ደስ አለን

(ጽጌ አብረሃም፣ ጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት፤ አዲስ አበባ)

ኳስ አዬ ኳስ ድቡልቡል
አንዴም ልብ ስትሰቅል
ስታሰጥም በሃሳብ ማእበል
ስታስፈነጥዝ በደስታ በርካታ
አየ . . . የእግር ኳስ ጨዋታ . . .
የሰሞኑ የልባችን ትርታ . . .
. . . የኳስ ቅብብል ጭውውት
አንዱ ሲያቀብል ሌላው ሲይዛት
. . . አቤት ሲያስደስት
በጭንቀት በሀሳብ መዋለል
የሞት ሽረት ትግል . . .
ጨዋታ . . . የኳስ ቅብብል
መሸነፍን መቀበል ተስኖን
ከኳሷ ጋር ዓይናችንን አንከራተን
ግባችን ተሰፋ ቆርጦ
በጨዋታ ዓለም ማሸነፍ መሸነፍ ስላለ
መቸም ምንም አይደለ
አ . . . እንዴት ሊሆን
ጭራሽ ለመቀበል አቅቶን
ኳስ ድቡልቡልነቷን ስተን
የተጫዋቾቻችን ድካም እየታሰበን
ኢትዮጵያ የዋንጫ ባለቤት መሆን
ማጣቱ ቆጭቶን . . .
ጎንበስ በኀዘን በንዴት
አየ . . . በአቻ ልታልቅ ትንሽ ሲቀራት
እ . . . እ . . . አይንን መፈታተን
ግብ . . . ግብ የመጨረሻ ገባችልን
ዳኘ ዳኘን . . .
አ! . . . ሆ . . . እንኳን ደስ አለን
ከልብ በላይ ፈነጠዝን
አሻሩን . . . አስደሰቱን
አስደሰቱን . . . አሻሩን
እንኳን ደስ አለን . . .
ዋንጫዋ ገባች በእጃችን።

**(አዲስ ዘመን ፣ ታህሳስ 22 ቀን 1980 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ በዩክሬን የተደረገውን ሄሊኮፕተር የመጥለፍ ሙከራ አከሸፍኩ አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩክሬን የሩሲያን "ሚ-8 ኤምቲፒአር -1" የውግያ ሄሊኮፕተር ለመጥለፍ ያደረገችው ሙከራ መክሸፉ ተሰማ፡፡ የሀገሪቱ የስለላ ድርጅት አባላት ሩሲያዊው አብራሪ ሄሊኮፕተሩን ለዩክሬን እንዲያስረክብ ከዛም 750 ሺ ዶላር እንደሚከፍሉት ሲያግባቡ ተደርሶባቸዋል፡፡

አብራሪው የደህንነት ሰዎቹ በቴሌግራም እንዳነጋገሩት፣ የተጠየቀውን የሚፈጽም ከሆነ ከሚከፈለው ገንዘብ ባለፈ የቼክ ሪፐብሊክ ፓስፖርት ተዘጋጅቶለት ከሀገር እንደሚያስወጡት ቃል እንደገቡለት ተናግሯል፡፡

ከዚህ ባለፈም "ሰርጌይ" በሚል የቴሌግራም ስም ሲያወራው የነበረው የዩክሬን የስለላ ድርጅት አባል አብራሪው ሄሊኮፕተሯን ወደ ዩክሬን ይዞ ከማምራቱ በፊት ባልደረቦቹን መመርዝ እንዳለበት እንደነገረው ገልጿል፡፡

ለዚህም በማንኛውም ፋርማሲ ውስጥ ሊገዙ የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን ያካተተ ገዳይ ድብልቅ በምግብ ውስጥ የሚጨምርበትን መመሪያም እንደተላከለት ይፋ አድርጓል፡፡

ሄሊኮፕተሩን ወደ ዩክሬን የሚወስድበትን ሂደት በተመለከተ በተሰጠው መመሪያም በቅድሚያ ወደ ቱርክ እንዲያቀና ከዛም ሞልዶቫ እና ፖላንድን አቋርጦ ዩክሬን ሲደርስ ለእርሱ እና ለቤተሰቦቹ የቼክ ሪፐብሊክ ፓስፖርት እና 750 ሺህ ዶላር እንደሚዘጋጅለት ተመላክቷል፡፡

የሩሲያ የፌዴራል ደህንነት አገልግሎት (ኤፍኤስቢ) ከአብራሪው የደረሰውን ጥቆማ ተከትሎ ሄሊኮፕተሩን ለመውሰድ የሚደረገውን ጥረት እስከ መጨረሻው ለማየት ወስኖ ከዩክሬናዊው ሰላይ ጋር ውስብስብ የሆነ የማጥመድ ጨዋታ ሲያደርግ እንደነበር ነው የተሰማው፡፡

ከደህንነት ተቋሙ ጋር በመነጋገር አብራሪው ሄሊኮፕተሩን ወደ ዩክሬን ለማምጣት መስማማቱን ተከትሎ የሚያርፍበትን ቦታ ካርታ እና ቀን የሚያመላክት መመሪያ ተልኮለታል፡፡

ሂደቱን እስከመጨረሻው የተከታተለው የሩስያ ደህንነት አገልግሎት በተጠቀሰው ቦታ ሄሊኮፕተሩን ለመቀበል ሲጠባበቁ በነበሩ የዩክሬን ወታደሮች እና የስለላ አባላት ላይ የሚሳይል ጥቃት መፈጸሙን ገልጿል።

በተጨማሪም ሰላዮቹ የሩስያ ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሮችን በመርዝ እና በተለያዩ መንገዶች ለመግደል ከብሪታንያ እና ሌሎች ምዕራባውያን የስለላ ድርጅቶች ጋር አብረው እንደሚሠሩ እንደተደረሰበት የሩሲያ የደህንነት አገልግሎት አስታውቋል፡፡

መሰል ጥረቶቹ አብራሪዎቹን በገንዘብ በማባባል ፣ በማስፈራራት እና ሌሎችም ዘዴዎችን በመጠቀም የሚጠየቁትን የሚያደርጉ ከሆነ አብራሪዎቹን እና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ፈለጓቸው የውጭ ሀገራት በመውሰድ ኑሯቸውን መመስረት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚችሉ እስከማስማማት ይደርሳል ተብሏል፡፡

አርቲ እንደዘገበው የተለያዩ የውግያ ሄሊኮፕተሮችን እና አውሮፕላኖችን ለመጥለፍ የዩክሬን ሰላዮች የሩሲያ ጦር አብራሪዎችን ለመደለል የሚያደርጉት ጥረት አሁንም ቀጥለዋል። ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ኤፍኤስቢ የሩሲያ አብራሪ "ቲዩ-22ኤም3" የተባለ ኒዩክሌር መሸከም የሚችል የጦር አውሮፕላን ወደ ዩክሬን እንዲበር ለማሳመን በኪቭ የተደረገውን ተመሳሳይ ያልተሳካ ሙከራ ማክሸፉ ተዘግቧል፡፡

## በአዘርቤጃን እየተካሄደ ባለው የኮፕ29 ስብሰባ

በጋዜጣው ሪፓርተር

ኮፕ29 የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ በአዘርቤጃን ዋና ከተማ ባኩ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በስብሰባው ላይ የተገኙት የኮፕ 28 ፕሬዝዳንት ዶክተር ሱልጣን አል ጃቢር በአሁኑ ወቅት ግጭቶች እና ክፍፍሎች መኖራቸውን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ ትብብር እና ውይይት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ዶክተር አል ጃቢር በኮፕ28 ስብሰባ ታሪካዊ የተባለው "የዩኤኢ ስምምነት" እንዲደረስ አድርገዋል ያሏቸውን የአረብ ኢምሬትስ ፕሬዝዳንት እና ስብሰባውን ያስፈጸሙትን ሠራተኞች አመስግነዋል።

ዶክተር ጃቢር አክለው እንደገለጹት ኮፕ 29 የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ወደተግባር የሚቀየርበት ነው።

በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ መሻሻሎችን ለማምጣት ፋይናንስ ወሳኝ መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ጃቢር ሁሉይም የመንግሥት እና የግል የፋይናንስ ምንጮች እንዲለግሱ ማበረታታት ይገባል ብለዋል።

ዶክተር ጃቢር ዓለም የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋት አንድ የጋራ ግብ እንዲያስቀምጥ እንደሚፈልጉም ገልጸዋል።



ዶክተር አል ጃቢር

ባለፈው ስብሰባ "በዱባይ ታሪካዊ የሚባል ስምምነት ላይ ደርሰናል። ነገር ግን ታሪክ የሚፈርደን በሠራነው ተጨባጭ ሥራ ነው" ብለዋል ዶክተር ጃቢር።

የተባበሩት ኤምሬትስ ከ100 ሺህ በላይ ሰዎች የተሳተፉበትን የመንግሥታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ በስኬት ማስተናገዷ የሚታወስ ነው።

# ስፖርት





# ኢትዮ ኤሌክትሪክ የ 30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር አሸናፊ ሆነ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በየዓመቱ ከሚያከናውናቸው የሀገር ውስጥ ውድድሮች ውስጥ አንዱ የ30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር ነው። ፌዴሬሽኑ የ2017 ዓ/ም የውድድር መርሃግብሩን ከትናንት በስቲያ በቢሾፍቱ ከተማ በዚህ የጎዳና ላይ ውድድር የጀመረ ሲሆን ኢትዮ ኤሌክትሪክ አጠቃላይ የውድድሩ አሸናፊ ሆኗል።

ትልቅ ስም ያላቸው አትሌቶች ጭምር በተፎካከሩበት የሴቶች ውድድር ትግስት ግርማ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ክለብ ቀዳሚ ሆና አጠናቃለች። ፅጌ ሃይለሥላሴ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ሁለተኛ፣ ሩቲ አጋና ሮዛ ደረጀ ከፌዴራል ማረሚያ ሦስተኛና አራተኛ ደረጃን ይዘው ፈፅመዋል። በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር ደግሞ ሃይለማሪያም ኪሮስ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ቀዳሚ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፣ አሰፋ መንግሥቱ በግል ሁለተኛ ሆኗል። ባየልኝ ተሻገርና አምባዬ ጎይቶም ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ሦስተኛና አራተኛ ሆነው ውድድሩን ጨርሰዋል።

በውጤቱ መሠረት ኢትዮ ኤሌክትሪክ በሴቶች በ22 ነጥብ 1ኛና የዋንጫ ተሸላሚ ሲሆን፣ ፌዴራል ማረሚያ በ24 ነጥብ 2ኛ፣ ኦሮሚያ ፖሊስ በ50 ነጥብ 3ኛ ደረጃን መያዝ ችለዋል። በወንዶችም ኢትዮ ኤሌክትሪክ በ19 ነጥብ 1ኛ የዋንጫ ተሸላሚ ሲሆን ኦሮሚያ ፖሊስ በ40 ነጥብ 2ኛ፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 76 ነጥብ 3ኛ ሆኖ አጠናቋል። በዚህም ኢትዮ ኤሌክትሪክ አጠቃላይ የውድድሩ አሸናፊ የሆነበትን ዋንጫ ወስዷል።

በወንዶች ቬትራን ከ50 ዓመት በላይ በተካሄደው ውድድር ገዛኸኝ ገብሬ አሸናፊ ሲሆን ስዩም ደበሌ ሁለተኛ፣ ደረጄ ገመቹ ደግሞ ሦስተኛ ደረጃ ይዘው አጠናቀዋል። በተመሳሳይ በቬትራን ሴቶች ከ50 ዓመት በታች አበሩ ዘውዴ አሸናፊ ስትሆን አዳነች ተስፋዬና እህተብርሃን አዳሙ ሁለተኛና ሦስተኛ ሆነው ማጠናቀቅ ችለዋል።






**አትሌት ትግስት ግርማ ፌደራል ማረሚያና አትሌት ሃይለማሪያም ኪሮስ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ውድድሩን አሸንፈዋል፣**

ከ1ኛ-3ኛ ያጠናቀቁ አትሌቶች የወርቅ፣ የብር እና የነሐስ ሜዳልያ የተሸለሙ ሲሆን እንደየደረጃቸው ከ40 ሺ. እስከ 18ሺ. ብርም ተበርክቶላቸዋል፡፡ ከ4-8 ያጠናቀቁ አትሌቶችም እንደየደረጃቸው ከ16ሺህ እስከ 8 ሺህ ብር ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከ1-6 ባለው ደረጃ ያጠናቀቁ የቬትራን አትሌቶችም ከ6ሺህ ብር እስከ 500 ብር እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት አግኝተዋል፡፡

የውድድሩ ዓላማ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ክለቦች፣ ተቋማትና የግል ተወዳዳሪ አትሌቶች የውድድር ዕድል ለመፍጠርና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት እንዲሁም አትሌቶችን በሽልማት ለማበረታታት መሆኑን ፌዴሬሽኑ ገልጿል፡፡

የውድድሩ ተሳታፊዎች ክልሎች፣ ክለቦች፣ እና በግል ተመዝግበው የሚወዳደሩ አትሌቶች እና አንጋፋ አትሌቶች ሲሆኑ በዘንድሮው ውድድር ላይ ሦስት ክልል አንድ ከተማ አስተዳደር፣ አስራ አምስት ክለቦች፣ አንጋፋ (ቬትራን) አትሌቶች እና በግል ተመዝግበው የሚወዳደሩ አትሌቶች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ 385 ወንድ ፣ 137 ሴት አትሌቶች በአጠቃላይ 522 አትሌቶች ተፎካካሪ ሆነዋል፡፡ ይህም ካለፈው ውድድር አንፃር በ 59 አትሌቶች የዘንድሮ ውድድር ተሳትፎው የበለጠ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ይህ የ 30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በ2001 ዓ.ም. በአዳማ ከተማ የመጀመሪያውን ውድድር በ115 ወንድ እና 28 ሴት በድምሩ 143 አትሌቶችን በማሳተፍ የተጀመረ ሲሆን፣ ለ10 ተከታታይ ዓመታት እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ በአዳማ ከተማ ሲካሄድ ቆይቶ እስከ 2010 ዓ.ም. ድረስ ውድድሩ ተቋርጦ በድጋሚ 7ኛውን እና 9ኛውን ውድድር በቢሾፍቱ ከተማ ሲደረግ 6ኛው ውድድር በ2012 በፌዴሬሽኑ የውድድር መርሃ ግብር ለማካሄድ በእቅድ ተይዞ በኮቪድ-19 ወረርሽን ምክንያት ተሰርዟል፡፡ ለ8ኛ ጊዜ ሊካሄድ የነበረው ውድድርም በሥራ መደራረብ ምክንያት ሳይካሄድ መቅረቱን ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ዘንድሮ ግን «11ኛው የ30 ኪሎ ሜትር የጐዳና ላይ ሩጫ» በሚል ስያሜ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቢሾፍቱ ከተማ በስኬት ተካሂዷል፡፡

## ትግራይ ክልል

የባለንብረት ስም ተመስገን ኪሮስ ተኩሉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-05864 ት.ግ ቻንሲ ቁጥር DH200-0029623 የሞተር ቁጥር 2KD-1364570 የሞዴል ቁጥር KDH200V-SMMY የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብሎ በ10/01 /2017ዓ/ም አመልክተዋል። ሰሌዳውን ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ መታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትእዛዝ እንድያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በትግራይ ክልላዊ መንግሥት የአድዋ ከተማ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ጽ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም፣ ግደይ ደስታ ገ/ዋህድ የተሽከርካሪው ዓይነት ድርብ ተግባር የሰሌዳ ቁጥር 03-63050 ኢት የሻንሲ ቁጥር MROBZ8CD700104465 የሞተር ቁጥር 1KDUB881354 ከላይ በመረጃው የተገለፀው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ የጠፋባቸው ለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ሲሆን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃን፡፡

**የመቀሌ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ድሬዳዋ አስተዳደር

የባለንብረቱ ስም አብዲ ከሊፋ መሀመድ የሠሌዳ ቁጥር 01-13868 ድሬ የተሽከርካሪው ዓይነት ትራይሳይክል የሻንሲው ቁጥር MC1AYCGBYEA003028 ሞዴል FORCE የሞተር ቁጥር D12103800 የሠሌዳ ቁጥር 01-13868 ድሬ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሠሌዳ የፊት የኋላ ጠፋብኝ ብለው በ18/02/2017 ዓ.ም ቀን አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ባለሥልጣን**

## አማራ ክልል

የባለንብረት ስም ማስተዋል መለስ ተወካይ ስሜነህ ፍቃዱ የሰሌዳ ቁጥር አማ 03-28989 የሻንሲ ቁጥር JTGSs22P2E0135211 የሞተር ቁጥር 2KD-A554189 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶብስ ሞዴል 2014 ከላይ ደረጃው የተገለፀው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪው የኋላ ስኬር ሰሌዳ ስለጠፋብኝ በ14/02/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን አመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም Dereje Abebe - የሰሌዳ ቁጥር OR-01-13215 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በ13/02/2017 አመልክተዋል፡፡

በዚሁ መሰረት የመኪና ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስተወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ለአመልካች ሰሌዳ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የአዳማ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የባለንብረቱ ስም ባከሪ አብዲ ኢሣ የሰሌዳ ቁጥር 1-A09375OR የሊብሬ ቁጥር 0331628 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ኦሪጅናል ጠፋብን ብለው በ20/02/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የባለቤትነት ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/አመልካች አቶ ተስፋዬ ነጋሳ ኢብሳ እና በተከሳሽ/ተጠሪ ወ/ሮ ግደይ ሐዲስ ተክሌ መካከል በፌ/መ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ17/03/2017 ዓ.ም ከቀኑ 4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም መሀደር ሹምዬ ተፈራ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A11745 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር JTDBW923781130575 ሞዴል NCP92L-BEMRKV የሞተር ቁጥር 2NZ-5105305 የሊብሬ ቁጥር 183771 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 25/2/2017 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የካ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ ጊዜወርቅ ብስራት ወልዴ እና በተከሳሽ አቶ እንዳልካቸው እስማኤል መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ13/03/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ/ምድብ 4ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ 1ኛ ስኬት ባንክ እና በተከሳሽ 1ኛ. ቢኒያም ተዘራ 2ኛ. ህሊና አበራ 3ኛ. ሄለን ሀብቴ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ን/ኢ. ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በ19/3/2017 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 6ኛ ባ/ኢ. ችሎት አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ደሳለኝ አስራደ ካሳ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A14595 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር LZZ5BLSF8NN957232 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47 220307024747 የሊብሬ ቁጥር 0244518 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 18/2/2017 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአራዳ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሜድሮክ ወርቅ ማአድን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-36784 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻሲ ቁጥር 654808 ሞዴል fh400 የሊብሬ ቁጥር E0092571 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 10/2/2017 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**